# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ለድህረ ምርቃ ፕሮግራም ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

**የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር ፍተሻ**

**በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት**


በ

አስረስ አበበ



ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ጅማ ዩንቨርሲቲ

# የአማርኛ  ቋንቋ መምህራን ለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር ፍተሻ

## በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ለድህረ ምርቃ ፕሮግራም ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

በ

አስረስ አበበ

የጥናቱ አማካሪዎች

ደመላሽ መንግስቱ (ዶ/ር)

በቃሉ ፈረደ (ተ/ፕሮፌሰር)



ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ጅማ ዩንቨርሲቲ

# የአማካሪዎች ይሁንታ

ተማሪ አስረስ አበበ ዘገዬ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ተማሪ ሲሆን መመረቂያ ስራውን ከአማካሪዎቹ ጋር በትብብር እየሰራ የቆየ ስለሆነ ለተቋቁሞ መቅረብ የሚችል መሆኑን እናረጋግጣለን ፡፡

ዋና አማካሪ ስም……………………………………ፊርማ……………….. ቀን…………

ረዳት አማካሪ ስም…………………………………ፊርማ…………………..ቀን…………

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ለድህረ ምርቃ ፕሮግራም ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

የአማርኛ  ቋንቋ መምህራን ለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር ፍተሻ

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት

በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ሟሟያነት በአስረስ አበበ ዘገዬ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ የዩኒቨርስቲውን የጥራትና ወጥነት መስፈርት በማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል ፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዋና አማካሪ ስም -------------------------------------------------------ፍርማ---------------------------

ረዳት አማካሪ ስም ------------------------------------------------------ፍርማ--------------------------

የውጭ ፈታኝ ስም  ---------------------------------------------------ፍርማ-------------------------

የውስጥ ፈታኝ ስም -------------------------------------------------------ፍርማ------------------------

# ምስጋና

በቅድሚያ ጥናቱ እዚህ ደረጃ ይደርስ ዘንድ ለረዳኝ ቸሩ እግዚአብሔር ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ፡፡ በመቀጠል ጥናታዊ ጽሁፌን በማስተካከል እገዛ ላደርጉልኝ አማካሪዎቼ ለዶ/ር ደመላሽ መንግስቱ እና ለተ/ፕሮፌሰር በቃሉ ፈረደ ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ነው፡፡

እንዲሁም ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ሳከናውን የተለያዩ አጋዥ መረጃዎችን እና ማስተካከያዎችን በመስጠት የተባበሩኝ ተ/ፕሮፌሰር አለማየሁ ተክለማሪያምና ከጎኔ በመሆን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የሞራል ድጋፍ ላደረጉልኝ ለውድ ቤተሰቦቼ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

በመጨረሻም የፅሁፍ መጠይቁን በመሙላት፣ ቃለ መጠይቁንና ምልከታው በተሳካ መንገድ አከናውኜ መረጃዎችን እሰበስብ ዘንድ ለተባበረኝ ውድ ጓደኞቼና በጥናቱ ተሳታፊ ለነበሩ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋን መምህራን በሙሉ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ቅይጥ የምርምር ስልት የተከተለ ሲሆን ንድፉም ገላጭ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በምስረቅ አርሲ ዞን በሚገኙ 102 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ5 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2013 ዓ.ም በማስተማር ላይ ካሉ አጠቃላይ 66 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ በቀላል እጣ ንሞናን ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ 33 መምህራን ናቸው፡፡ ለጥናቱ የዋሉ መረጃዎች የተሰበሰቡት በፅሁፍ መጠይቅ፣ በምልከታና በቃለመጠይቅ ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነታዊ በሆነ መንገድ በገለፃ የተተነተኑ ሲሆን በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመቶኛ ስሌት ተተንትነዋል ፡፡ በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደ አይነታቸው በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስትና በገለጻ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በትንተናው መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ አማካይ ውጤት (2.48) ሲሆን ከፍተሸ ዋጋ አማካይ ውጤት (2.5) ጋር ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ መካከለኛ እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በተጨማሪም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ሲታይ የተገኘው አማካይ ውጤትም (2.49) ሲሆን ከፍተሻ ዋጋ (2.5) ጋር ሲነፃፀር ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቶ ትምህርት አተገባበር መካከለኛ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ትግበራን መሰረት አድርጎ በተከናወነው ከክፍል ምልከታ የተገኘው ውጤት 57% መምህራን የምልከታ መቆጣጠሪያ ቅፅ ተግባራትን እየተገበሩ ሲሆን 43% አልተገበሩም፡፡ ይህ ውጤት እንደሚያሳየው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር መካከለኛ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአይነታዊ በሆነ መንገድ ተተንትነዋል ፡፡ በትንተናውም መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ አካቶ ትምህርት በተማሪዎች መካከል እኩልነት ለማስፈን የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አለመረዳት፣ የስራ ላይ ስልጠና አለመሰጠት፣ በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እገዛ የአካቶ ትምህርት በበቂ ሁኔታ መስጠትን አለመረዳት፣ አመቺና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በበቂ ሁኔታ አለመጠቀም ፣የተለያዩ መርጃ መሳሪያ እንበዛም አለመጠቀም፣ የተማሪዎችን ስብጥር በበቂ ሁኔታ ግምት ውስጥ አለማስገባት፣ የቁጥጥር አካል ክትትልና ድጋፍ እንብዛም አለማድረግ የሚሉተን ጥናቱ አሳይቷል ፡፡በመጨረሻም ችግሩን ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሔ ሀሳቦች ተጠቁመው ጥናቱ ተጠቃሏል

# ማውጫ

ይዘት ገፅ


ምስጋና....................i

አጠቃሎ....................ii

ምዕራፍ አንድ....................1

1፡ መግቢያ....................1

1.1. የጥናቱ ዳራ....................1

1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር....................3

1.3. የጥናቱ ዓላማ....................5

1.4. አስፈላጊነት....................5

1.5. የጥናቱ ወሰን....................6

1.6. የጥናቱ ውስንነት....................6

1.7.የቁልፍ ቃላት ብያኔ....................7

ምዕራፍ ሁለት....................8

2፡ ክለሳ ድርሳናት....................8

2.1. የአካቶ ትምህርት ምንነት....................8

2.2. የአካቶ ትምህርት አጀማመር....................11

2.3. የአካቶ ትምህርት በዓለምና በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የህግ ማዕቀፍ....................13

2.4. ቋንቋና የአካቶ ትምህርት....................16

2.5. የመምህራን አካቶ ትምህርት ግንዛቤ....................17

2.6. የመምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር....................20

2.7. በመምህራን የአካቶ ትምህርት አመለካከትና ትግበራ ላይ አሉታዊ ሁኔታ የሚያሳድሩ ተፅዕኖዎች....................21

2.8. በመምህራን አካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ የሚገጥሙ ተግዳሮቶች....................24

2.9. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት....................27

ምዕራፍ ሶስት....................29

3፡ የአጠናን ዘዴ....................29

3.1. የጥናቱ ስልት....................29

3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች....................29

3.3. መረጃ መስብሰቢያ መሳሪያዎች....................29

3.3.1.የፅሑፍ መጠይቅ....................29

3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ....................30

3.3.3. ቃለ መጠይቅ ..... 31
3.4. የጥናቱ ሂደት ..... 31
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 32
ምዕራፍ አራት ..... 33
4፡ የውጤት ትንታናና ማብራሪያ ..... 33
4.1. የታጣኚዎች ግለ-ማንነት ..... 33
4.2. የውጤት ትንተና ..... 34
4.2.1 ከፅሁፍ መጠይቅ ግንዛቤና አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና ..... 34
4.2.1.1 ከፅሁፍ መጠይቅ ግንዛቤን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና ..... 34
4.2.1.2 ከፅሁፍ መጠይቅ አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና ..... 37
4.2.2 ከቃለ መጠይቅ ግንዛቤና አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና ..... 40
4.2.2.1 ከቃለ መጠይቅ ግንዛቤን የተመለከ የተገኘ ውጤት ትንተና ..... 40
4.2.2.2 ከቃለ መጠይቅ አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ የውጤት ትንተና ..... 41
4.2.3 በክፍል ምልከታ አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና ..... 41
4.2.4. የግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ አድራሾች የተገኘ ውጤት ትንተና ..... 43
4.3 የውጤቱ ማብራሪያ ..... 44
ምዕራፍ አምስት ..... 47
5፡ ማጠቃለያ፣ መደምደምያና አስተያየት ..... 47
5.1. ማጠቃለያ ..... 47
5.2. መደምደምያ ..... 48
5.3. አስተያየት ..... 49
ዋቢዎች ..... 51
አባሪዎች ..... 56
አባሪ ሀ፡ የፅሑፍ መጠይቅ ..... 56
አባሪ ለ፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ ቼክሊስት ..... 60
አባሪ ሐ ፡ቃለ መጠይቅ ..... 62
አባሪ መ፧ የፅሑፍ መጠይቅ ውጤት ..... 64
አባሪ ሠ፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት ..... 66

# ምዕራፍ አንድ

# 1፡ መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በአካቶ ትምህርት መርሃ ግብር መጀመሪያ ትኩርት ይሰጥ የነበረው በአብዛኛው ለልዩ ፍላጎት ነበር Regmi (2017)፡፡ Jordan Carlile & Stack (2008) እንደገለፁት በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተለይም አዕምሯዊና አካላዊ የሆነ ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ልዩ እገዛ እንደ ሚያስፈልጋቸው ሙያዊ የሆነ እይታ ብቅ እያለ መጣ፡፡ በመቀጠልም በዘመናዊ እይታ አካል ጉዳተኞቹን የማገገዝና የመደገፍ ሁኔታ ከፖለቲካዊ እይታ አንፃር በመመልከት ከሰብአዊ መብቶች ውስጥ እንደ አንዱ መታየት ተጀመረ፡፡ በተወሰነ መልኩ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችን በመለየት በትምህርትና በስራ ዕድል ክፍተቶች እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እኩል አለመሳተፋቸውን ታሳቢ በማድረግ ድጋፍ ይሰጣቸው ጀመር፡፡

Greene (2017) እንደጠቀሱት ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ የተለያዩ ስምምነቶች በመፍጠር በተለይም የማየት ችግር ላለባቸው ልጆች የተለያዩ የትምህርት አቀራረቦችን መዘርጋት ተጀመረ፡፡ የማህበረ ባህላዊ ፍልስፍናና የህክምና እውቀት ባለሙያዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ስለአካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ በመፍጠር በትምህርት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጥረዋል፡፡ በሌሎች የተወሰኑ ሙያዊ ተቋማትም ትምህርት ለአካል ጉዳተኞች እንደ መብት ተደርጎ እንዲታሰብ በማድረግ ልዩ የቀን ትምህርት ቤቶች ልዩ ክፍሎችን አዘጋጅተው ተሳታፊ እንዲሆኑ አድርገዋል (Mastroieri & Scruggs 2001 ) ፡፡ Al-Katteeb (2002) እንደሚያብራሩት በፊት በነበሩት ዘመናት ለመማር በጣም ከባድ (Learnig Difficultis) የሆነባቸው ተማሪዎች ተለይተው በልዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ልዩ ትምህርት ይሰጣቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ተማሪዎቸ ለይቶ በልዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ማስተማሩ ያለውን ውጤታማነትን የተሻለ መሆኑን የሚያመላክት ምንም አይነት አሳማኝ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ስለዚህ ይህን የትምህርት አሰጣጥ ወደ ሌለ ለመቀየር ተፈለገ፡፡ በተከታታይም ህዝቡ በሚሰጠው አስተያየትና በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ለመማር ከባድ የሆነባቸውን ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተካተው በታላሚ ትምህርት ቤቶች (Mainstream schools) እንዲማሩ ታቀደ፡፡ የትምህርት አሰጣጡ በስፋት እየተተገበረ መጣ፡፡ ስያሜውን ወደ አካቶ ትምህርት በመቀየር ወቅታዊና አነጋጋሪ ጉዳይ እየሆነ መጣ Jordan Carlile & Stack (2008)

ለአካቶ ትምህርት የተለያዩ ብያኔ የተሰጠ ቢሆንም የተለያዩ ምሁራን የትምህርት አሰጣጥ ካለው ጠቀሜታ አንፃር በመደገፍና በመቃወም ሃሳባቸወን ሰንዝረዋል ፡፡ MastroPieri & Scruggs (2001) የትምህርት አሰጣጡን በመደገፍ አካቶ ትምህርት ልዩ ፍላጎት ያለቸውን ተማሪዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ተማሪዎች ጋር እንዲገናኙ ዕድል በመፍጠር ተማሪዎቹ ከመማር ሂደታቸው በተጨማሪ ማህበራዊ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠቅማቸዋል፡፡ በማለት ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይ Salend & Duhaniy (1999) ይህን ሃሳብ በመደገፍ እንዳብራሩት አካቶ ትምህርት የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ማህበራዊ ተቀበይነት እንዲያገኙ፣ የጓደኝነት ስሜት እንዲኖቸውና በመማር ተግባራቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድል ይፈጥራል፡፡ በሌላ መልኩ ይህን ሃሳብ በመቃወም Lyoyd,wilton & Townsend (2000) Baker & Zigmoud (1995) ሲገልፁ የአካቶ ትምህርት ፕሮግራም ለሁሉም የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች እየጠቀመ አይደለም፡፡ ለአብነትም አንዳንድ መጠነኛ የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ልዩ የሆነ የትምህርት መማሪያ ብቃት ባለው መልኩ አይዘጋጅም፡፡ በማለት ትችት ሰንዝረዋል፡፡

አካቶ ትምህርት በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘና እንደ ሰብአዊ መብት እየተቆጠረ ያለ ሲሆን ከትምህርት ሂደትም ባለፈ ድህነትን ለመቀነስና ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማሻሻል ወሳኝነት አለው (ካሴ 2013) ፡፡ እንደ Marchiesi (1998) ገለፃ አካቶ ትምህርት በተለያዩ አገራት አንድ ተቀባይነት ለማግኘቱ ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ውስጥ ተማሪዎች ለራሳቸው ያላቸው ግምት ከፍ እንዲል ማድረጉ፣ የሌሎችን ማህበራዊ ስብጥር እንዲያደንቁ ማስቻሉ፣ እንዲሁም ስለማህበራዊ ፍትህና እኩልነት ሰፊ ዕውቅና እንዲኖራቸው ማድረጉ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው ፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ አካቶ ትምህርት እንዲተገበር ትልቅ ተፅዕኖ ከፈጠሩ ነገሮች መካከል የዓለም አገራት ስምምነት ዋነኛው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶቸና ድንጋጌዎችን እንዲሁም ትምህርት ከሰብዓዊ መብቶች አንዱ መሆኑን አምኖ ተቀብሏል Minister of Education (2016)፡፡ የ1994ቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ አዋጅ ለሁሉም ዜጎች ጥራት ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ማዳረስ ከመብት ባለፈም ለመስረታዊ እድገት ዋስትና መሆኑ Minister of Education (2016) ገልፃል ፡፡ እንደ Minister of Education (2016) ገለጻ በኢትዮጵያ የአካቶ ትምህርት ስልጠና በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ መርሀ ግብር፣ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃና በሶስተኛ ዲገሪ ደረጃ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎ ይሰጣል፡፡

ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶት ትምህርት  ግንዛቤና አተገባበር ላይ የሚያተኩር ሲሆን መነሻው ሩሲያዊው የስነ ልቦና ተመራማሪ Vygostky በሚያራምደው ማህበረ ግንባታዊያን (Social Constructionism) ንድፈ ሃሳብ የተመሰረተ ነው፡፡Kitrian (2006) እንደሚያብራራው የማህበረ ግንባታዊያን ንድፈ ሃሳብ Vygostky በ1930ዎች በሶቭይት የጀመረው ሲሆን በስፋት ዕውቅና እያገኘ የመጣው በ1960ዎችና በ1970ዎቹ ነው፡፡ እንደ Vygostky እይታ አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሰዎች ማህበራዊና የተሰባጠረ የህይወት ልምድ በጣም ጥሩ እንደሆነ ይደግፋል፡፡ በማህበረ ግንባታውያን ንድፈ ሃሳብ አካል ጉዳተኛ ሰዎች ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር (ስብጥራዊ) ሂደት አማካይነት ማህበረ ባሕላዊ ህይወታቸውን ያሳድጋሉ Vygostky (1993)፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Ruvinshtion (1979) እንደ ጠቀሱት ማህበራዊ መስተጋብር ለአካል ጉዳተኛ ሰዎች በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የማህበራዊ ሁኔታ ዕድገት ለአካቶ ትምህርት በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በቫይጎስኪ ንድፈ ሃሳብ በመማር ሂደት ላይ መምህራን ተማሪዎችን ማገዝ አለባቸው፡፡ ይህ የመስተጋብር ክልል ‹‹የተቀራረበ የዕድገት ክልል›› (Zone of proximal Development) የሚል ስያሜ ተሰጥቶታ፡፡ የመምህራን ዕገዛ የሚደረግላቸው ተማሪዎች ከማይደረግላቸው ተማሪዎች በተሸለ መልኩ የመማር ግባቸውን ማሳካት እንደሚችሉ ይገልፃል፡፡

## 1.2. የጥናቱ መነሻ ችግር

የመምህራንን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበርን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ ለአብነትም Scruggs & Mastroper (1996) ባደረጉት ጥናት እንደጠቆሙት መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ግንዛቤ ቢኖራቸውም ነገር ግን በቂ ጊዜ ካለመኖር፣ የስራ ላይ ስልጠና ካለመሰልጠንና ግብዓቶች ካለመሟላት የተነሳ መምህራኑ የአካቶ ትምህርት ትግበራውን እንዳልፈፅሙ ገልፀዋል፡፡

Gokder (2012) በመጀመሪያ ደረጃ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ፣ ትኩረትና መስተጋብር ሂደት ላይ መሰረት አድርገው ባከናወኑት ጥናት እንደገለፁት የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ለማሻሻል የስራ ላይ ስልጠና ሲሆን ለትምህርቱ ጥራትም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ ጠቁመዋል ፡፡

አካቶ ትምህርት በተለያዩ ደረጃዎች በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ በተሳካ መልኩ አይተገበርም፡፡ ከነዚህም ውስጥ የአካቶ ትምህርት ፅንሰ ሃሳብን በሚገባ ተረድቶ አውንታዊ ግንዛቤ በተለያዩ አካላት አለመፈጠሩ አንዱ ምክንያት ነው Gokder (2013)፡፡ ይህን በመደገፍም Armstrong እና ሌሎች(2011) በጥናታቸው እንደጠቀሱት መምህራን ስለአካቶ

ትምህርት በቂ የሆነ ዕውቀት አለመያዛቸውና የተሳሳተ ግንዛቤ መኖሩ የተማሪዎችን ልዩነት ታሳቢ አድርገው ትምህርቱን እንዳይተገብሩ አድርጓቸዋል፡፡

እንደ አስራት (2013) ጥናት አካቶ ትምህርት ትግበራ እንዳይሳካ ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል በቂ ቁሳቁሶች አለመሟላት፣ መምህራን በቂ የስራ ላይ ስልጠና አለማግኘታቸውና የተለያዩ ደጋፊ አካላት አለመኖራቸው ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት መምህራን አካቶ ትምህርትን በተሳካ መንገድ እንዳይተገብሩ የሚያደርጋቸው የተለያዩ ውጤቶች ታይተዋል፡፡ ለአብነትም Fuchs (2010) እንደገለፀው መምህራን በቂ የትምህርት ዝግጅት አለማድረጋቸውና የስልጠና ማነስ ለአካቶ ትምህርት ትግበራ ውድቀት መነሻ መሆኑን በጥናታቸው ጠቁመዋል፡፡

በሌላ መልኩ Eoriin (1999) ባከናወኑት ጥናት እንደጠቀሱት መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት ያላቸው ዕውቀት አናሳ መሆኑና የተለያዩ ሙያዊ ድጋፎችን አለማግኘታቸው አካቶ ትምህርት በተሳካ መንገድ እንዳይተገብር ማድረጋቸውን ገልፀዋል፡፡

Alhassan (2014) በጋና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና ትግበራን በተመለከተ ባከናወኑት ጥናት እንደ ገለፁት መምህራን አዎንታዊ ግንዛቤ ቢኖራቸውም ነገር ግን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ዕውቀታቸው ዝቅተኛ እንደሆኑ ጠቁመዋል፡፡ ፦

ይህ ጥናት አንድም በአካቶ ትምህርት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከአገር ውስጥ ጥናቶች አንፃር ከተፈራ (1999)፣ ከጥሩሰው (2006)ና ከካሴ (2013) ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በሌላ በኩል በመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከታደሰ (2014) ጥናት ጋር ይቀራረባል፡፡ ከውጭ አገር ጥናቶች ጋር ሲታይ ከAlhassan (2014)ና ከGreen (2017) ጥናት ጋር ይዛመዳል፡፡ ከነዚህ ሁሉ ጥናቶች በዋናነት መምህራን ስለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ብቻ ያላቸውን ግንዛቤና የአካቶ ትምህርት አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል በመፈተሽ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም ከነዚህ ጥናቶች የሚለየው መምህራን የተማሪዎችን ልዩነቶች ( በባህል፣ በቋንቋ፣ በፆታ፣ ወዘተ )ሙሉ ታሳቢ አድርገው ከመገንዘብ እና አካቶ ትምህርትን ከመተግበር አኳያ ውጤቱ ምን እንደሚመስልና ተፅዕኖ አድራሾችን በመፈተሽ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ሃሳቦች መሰረት በማድረግ አጥኚው ሁለት አብይ ምክንያቶችን ይዞ ይህን ጥናት ለማጥናት ተነስቷል፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት ጥናቱ በሚጠናባቸው

አካባቢ ለመምህራን አካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ በቂ የሆነ ጥናት አለመጠናቱ ሲሆን ሁለተኛ ምክንያት በመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች እንዳመለከቱት ወጥ የሆነ ውጤት አለመታየቱን በመመልከት እነዚህን ጉዳዮች ጥናቱ ከሚጠኑባቸው ትምህርት ቤቶች አንፃር ምን ይመስላል? የሚለውን አጥኚው ለመመርመር ካለው ፍላጎት የተነሳ ነው፡፡

ይህ ጥናት የሚመልሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት ምን ያህል ግንዛቤ አላቸው?
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ምን ይመስላል?
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህርን  የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ተፅእኖ አድራሾች ምን ምንድናቸው?

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራ በአካቶ ትምህርት ላይ ያላቸው ግንዛቤ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል መመርመር
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራ በአካቶ ትምህርት ላይ ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ አድራሾችን እነማን እንደሆኑ መፈተሽ

## 1.4. አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ፈትሾ በማሳየት መረጃ ይሰጣል ፡፡ መረጃው ለመምህራን፣ ለትምህርት ባለሙያዎችና ለተመራማሪዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤቸውንና አተገባበራቸውን ምን እንደሚመስል ለይተው በማወቅ ወደፊት መሻሻል ያሉባቸው ነገሮች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ መረጃ ሊሰጥ ይችላል ፡፡

2. የትምህርት ባለሙያዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ምን እንደሚመስል በመገንዘብ ወደፊት ትግበራው ስኬታማ እንዲሆን መወጣት ያለባቸውን ሀላፊነት ለይተው እንዲያውቁ መረጃ ሊያገኙበት ይችላል ፡፡
3. የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበርን መሰረት አድርገው ወደፊት ሰፋ ያለ ምርምር ማካሄድ ለሚሹ ተመራማሪዎች መነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል ፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በምስራቅ አርሲ ዞን ካሉት 102 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ5 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው ፡፡ እነዚህም ትምህርት ቤቶች አሚኛ ገስጋር ፣ በሌ ገስጋር ፣ ሴሩ አባስ ፣ሮቤ ዲደአ እና ዲክሲስ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ የጥናቱ ተተኳሪዎችም በ2013 ዓ.ም በተጠቀሱት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ 66 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ ወንድ 25 ሴት 8 በድምሩ 33 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ብቻ በማተኮር ተከናውኗል፡፡

የጥናቱ ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር መፈተሽ ስለሆነ አጥኚው ጥናቱን ለማከናወን የተጠቀመባቸው ተላውጦዎች ሶስት ናቸው፡፡ እነዚህም አካቶ ትምህርት፣ ግንዛቤና አተገባበር ናቸው፡፡ ጥናቱ ውስጥ የተካተቱ ተሳታፊዎችም እነዚህ የትምህርት ቤት ደረጃዎች ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብቻ ናቸው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ብቻ በመሆኑ የአጠቃይ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ለመገምገም አያስችልም፡፡ በተጨማሪም በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ የተሰሩ በርካታ ጥናቶች ማግኘት አለመቻሉ የጥናቱን ውጤት ከቀደምት የአገር ውስጥ ጥናቶች ጋር ለማነፃፀርና ልዩነቱን በስፋት ለመመልከት አያስችልም፡፡ በተጨማሪም አጥኚው ከሚኖርበት አካባቢ ወቅታዊ ችግር ማለትም በCovid 19 የተነሳ ወደ ተለያዩ ትምህርት ቤቶች በመንቀሳቀስ በአርሲ ዞን በሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በጥናቱ አሳትፎ የአካቶ ትምህርት ግንዛቤቻቸውንና አተገባበራቸውን ለመፈተሽ አለመቻሉ አንፃራዊ በሆነ መልኩ የጥናቱ ውስንነት ሊያመላክት ይችላል፡፡

## 1.7.የቁልፍ ቃላት ብያኔ

አካቶ ትምህርት፣ ግንዛቤና አተገባበር የጥናቱ ቁልፍ ፅንሰ ሀሳች ናቸው። ተግባራዊ ብያኔያቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል።

1 አካቶ ትምህርት ፡- በመደበኛ ክፍል ውስጥ የተለያዩ አካል ጉዳተኞች፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ እምነት፣ ዘር፣ የትምህርት አቀባበል ወ.ዘ.ተ. ያላቸውን ተማሪዎች አጣጥሞ ማስተማር

2 ግንዛቤ፡- የመደበኛ ክፍል መምህራን የተለያየ ዳራ ያላቸውን ተማሪዎች አካቶ በማስተማር ላይ ያላቸው አመለካከት ሲሆን በፅሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የሚለካ

3 አተገባበር፡- የመምህራን አካቶ ትምህርት አከዋወን ሲሆን በፅሁፍ መጠይቅና በምልከየሚለካ

# ምዕራፍ ሁለት

# 2፡ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የአካቶ ትምህርት ምንነት

አካቶ ትምህርት የሁሉንም ተማሪዎች ስብጥራዊ የመማር ፍላጎት፣ ባህሎችንና ልዩነቶችን መሰረት በማድረግ ማግለልን ቀንሶ በትምህርት ውስጥ ሁሉን ማሳተፍን የሚመለከት ነው። እንዲሁም ሁሉም ተማሪዎች እንደ ፍላጎታቸው መማር የሚችሉበት፣ በመማር ላይ ያሉ ልዩነቶች የሚጠቡበት፣ የተማሪዎች ልዩነት በተመለከተ የግንዛቤና የባህሪ ማሻሻያ የሚደረግበት፣ የማስተማሪያ ዘዴና ስርዓተ ትምህርቱ ተግባራዊ የሚሆንበት ነው Unesco (2003)። እንደ Pijil, Meijer & Hegarty (1997) ገለፃ አካቶ ትምህርት የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በመደበኛ ክፍል ውስጥ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ የሚያግዝ ነው።

Tomas, Walker & Webb (1998) እንደሚያስረዱት አካቶ ትምህርት የተለያየ ችሎታ፣ ቋንቋ፣ ፆታ፣ ጎሳ፣ ባህላዊ ዳራ ያላቸውን ተማሪዎች ሁሉ በትምህርት ቤት ውስጥ እኩል የሚያሳትፍና ዕድል የሚሰጥ ነው። በሌላ መልኩ Unesco (2005) እንደጠቀሰው አካቶ ትምህርት ግለሰባዊ ልዩነቶችን እንደ ችግር የሚመለከት ሳይሆን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለተማሪዎች ስብጥራዊ ሁኔታ ምላሽ የሚሰጥ ነው። አካቶ ትምህርት የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ማህበራዊ ተቀባይነት እንዲያገኙ፣ የጓደኝነት ስሜት እንዲኖራቸውና በመማር ተግባራቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ እድል ይፈጥራል Salend & Duhaneyl (1999)::

በተመሳሳይ Pijil,Mojrel & Hegarty (1997) እንደገለፁት አካቶ ትምህርት በትምህርት አሳቤ ውስጥ ሲታይ ሰፊ የተማሪዎች ስብጥር የያዘና ለስብጥሩ የተለየዩ ትምህርቶች የሚቀርብበት ነው፡፡ Raser(2008) እንደሚስረዱት አካቶ ትምህርት ሁሉን ተማሪዎች ግምት ውስጥ ማስገባትን ፣ የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግን ፣ ከባህል አንፃር መገለልን መቀነስ የሚመለከት ሲሆን ከስረአተ ትምህርቱና ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አኳያ አካል ጉዳተኞችን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ልዩነቶችም ታሳቢ የሚያደርግ ነው::

በስነ ትምህርት እንደዚሁም በሌሎች ተዛማጅ የትምህርት መስኮች ፣ ለአብነት በስነ ባህርያዊ ፣ በፍልስፍና ፣ በማህበራዊና እና በመሳሰሉት ፣ምሁራን የሆኑ ግለሰቦች እንደገለፁት ፣ ትምህርት የሰው ልጆች በመሠረታዊነት የሚታይ መብት ሲሆን ፣ ብሎም ማህበረሰብን በሁሉም የህይወት ዘርፍ የኑሮ ሁኔታ ብቃትን በማላበስ ምርታማ የሚያደርግ የአገልግሎት ዓይነት ነው:: ከዚህ የተነሳም ፣ ሁሉም የሰው ልጆች ያለ አድልዎ በትምህርት ሂደት ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል፤ በተያያዥነት፣ በእንዲህ ዓይነት የትምህርት አሰጣጥ አውድ

የአካቶ ትምህርት ሲጠቀስ ፣ ምንነቱን እንደዚሁም አተገባበሩ ምን መምሰል እንዳለበት በጥልቀት መታየት እንዳለበት ይገልፃል (UNESCO ፡ 1994)።

የአካቶ ትምህርት በጥቅሉ ሁሉንም ልጆችና ወጣቶች በእኩል ዓይን የሚመለከት የመማር ክንውን ሲሆን ፣ በዝርዝር ሲታይ ደግሞ የተለያዩ የአካል ጉዳትም ሆነ ሌሎች ችግሮች ያሉባቸውን ወገኖች ፣ እንደዚሁም ሌሎች ተማሪዎችን ባቀናጀ መልኩ ለሁሉም እንደ የፍላጎታቸውና ችሎታቸው የመማር ማስተማር ዘዴዎችን በመምረጥ ትምህርት የሚሰጥበት ሁኔታ ብቻም ሳይሆን ብዙሃነትን በሚገባ መረዳት የሚሻ የትምህርት አሰጣጥ ሂደት እንደሆነ Salend & Duhaney(1999 ) ጠቅሰዋል ።

እንደ Armstrong ( 2004 ) ገለፃ አካቶ ትምህርት በተመለከተ የተለየዩ ንድፍ ሃሳባዊ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ብያኔዎች ተሰንዝረዋል። ይህም ከመብት (right) ከውጤታማነት ( Effective ) ከፖለቲካ (Poltical) ከተግባራዊ ሁኔታ አንፃር ብያኔዎች ተሰንዝረዋል። የአካቶ ትምህርት ብያኔ ከፖለቲካ አኳያ በትምህርት አሰጣጥ ትክክለኝነትንና ማህበራዊ መፍትሄን በማስፈን ላይ ያተኮረ ነው ። ከዚህ ጋር በተያያዘ Johnstone (2007)ና Green(2017) እንደጠቆሙት አካቶ ትምህርት ከፖሎቲካ አላማ ሲታይ ዲሞክራሳዊና ፍህታዊ ማህበረሰብን መፍጠር ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

Marchiesi (1998) በውጤታማነት አንፃር አካቶ ትምህርት ወጪ ቆጣቢ የትምህርት አሰጣጥ ነው። በማለት ሲበይኑ በሌላ መልኩ ከተግባራዊ እውነታ አኳያ አካቶ ትምህርት በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ዘንድ የማካተት ትግበራና የባህል ትስስሮሽ የሚፈጥር ነው ። ተብሎ ተበይኗል ።

Unianu (2011) ሲገልፁ አካቶ ትምህርት በትምህርት እሳቤ ውስጥ ሲታይ ሰፊ የተማሪዎች ስብጥር የያዘና ለስብጥሩ የተለያዩ ትምህርቶች የሚቀርቡበት ነው። Thomas, Walker & Webb (2005) እንደጠቀሱት አካቶ ትምህርት የተለያዩ ችሎታ፣ ቋንቋ፣ ፆታ፣ ጎሳ፣ ባህላዊ ዳራ ያላቸውን ተማሪዎች ሁሉ በትምህርት ቤት ውስጥ እኩል የሚያሳትፍና ዕድል የሚሰጥ ነው። Rise (2008) እንደሚያስረዱት አካቶ ትምህርት ሁሉን ተማሪዎች ግምት ውስጥ ማስገባትን የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግን ከባህል አንፃር መገለልን መቀነስ የሚመለከት ሲሆን ከሰርኣተ ትምህርቱና ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ አኳያ አካል ጉዳተኞችን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ልዩነቶችም ታሳቢ የሚደረግበት ነው።

Mastroieri & Scruggs (2001)ን በዋቢነት ጠቅሰው Jennifer (2015) እንደገለፁት ስኬታማ አካቶ ትምህርት የሚከተሉትን ባህሪያት ያንፀባርቃል። በየደረጃው አስተዳደራዊ

የሆነ ድጋፍና ግንባታ የሚከናውኑበት ነው። በተጨማሪም የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንና አባላት ዕቅድ በማዘጋጀት፣ በህብረት በማስተማርና መመሪያዎን ማለማመድ ረዳት ሆነው የሚተውኑብት ነው። ከዚህ ባለፈም የተማሪዎችን ልዩነት አምኖ በመቀበል በክፍሉ ላይ አዎንታዊ መንፈስ እንዲታይ የሚያደርግ በስርዓተ ትምህርቱ ላይ በማተኮር የቀረበውን ይዘት ተጨባጭና ትርጉማዊ በማድረግ የሚተገበር የክፍሉ መምህር በሌሎች አጋዥ መምህራን አማካይነት በማስተማር ክህሎት፣ በአቀራረብ፣ ከግልዕነት አኳያ፣ ከትጋትና የማስተማር እንቅስቃሴውን ወደፊት ከማራመድ አንፃር ውጤታማ የሚሆነበት ነው።

Forlin, cedillo, Romero, Fletcher & Hemandez (2010) ሲገልፁ አካቶ ትምህርት በአጠቃላይ በትምህርት ውስጥ አካል ጉዳተኞችን ከማካተቱ በተጨማሪ ትከረቱን በማስፋት ትምህርትን ዓላማ የማድረግ ውጤታማ የማስረዳት ክህሎት የሚታይበት ነው። እንዲሁም የሁሉን ተማሪዎች ልዩነት ታሳቢ እያደረገ የመጣ ነው። Unisco(2005) እንደጠቀሰው አካቶ ትምህርት ግለሰባዊ ልዩነቶችን እንደ ችግር የሚመለከት ሳይሆን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለተማሪዎ ስብጥራዊ ሁኔታ ምላሽ የሚሰጥ ነው።

አካቶ ትምህርት በቅድሚያ አካል ጉዳተኝነትን ታሳቢ አድርጎ መነሳቱ ለመርሀ ግብሩ ዕድገት በጣም ከፍተኛ ሚና ነበረው። በአሁኑ ወቅት የአካቶ ትምህርት ትኩረት በአካል ጉዳተኞች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የሁሉንም ተማሪዎች ልዩነት ታሳቢ በማድረግ መማር የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር ላይ የተመሰረተ ነው Regmi (2017)። Unisco (1994) እንደገለፀው አለም አቀፋዊ የአገራት ስምምነት ለአካቶ ትምህርት ዕድገት ትልቅ ሚናን ተጫውቷል።

የአካቶ ትምህርት ሊኖረው የሚገባውን የአቃፊነት ባህርይ አስመልክቶ 1994ቱ የሰፔን የሰላም አለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 7 ሁሉም ህፃናት ያላቸውን ልዩነትና ሌሎች ተግዳሮቶች ወደ ጎን በመተው በቅንጅት በመተባበር መማር እንደሚገባቸው ፣ በተጓዳኝም የአካቶ የትምህርት አሰጣጥ የማንኛውም ተማሪ የተለያዩ ፍላጎቶችና ችሎታዎች ያገናዘቡ ፣ ከዚህ ባለፈም ለተማሪዎች ተስማሚ የመማር አውድ እንደዚሁም የማስተማሪያ ዘዴ መፍጠ ር እንዳለበት ሲገለጽ፣ በአጠቃላይም ጥራት ያለውን የትምህርት ተደራሽነት ለማቅረብ በስርአተ ትምህርት ፣ በተቋማት ግንባታ  በማዋቅር ዝርጋታ እና በመማር ማስተማር ዘዴ ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል (UNESCO : 2003) ::

ከላይ በቀረቡት የአካቶ ትምህርት የተመለከቱት ጽንሰ ሀሳቦች መነሻነት ፣ በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞችም ሆኑ ሌሎች ማህበራዊና ስነልቦናዊ ችግር ያለባቸው ልጆች ወዘተ

ከተጋረጡባቸው ተግዳሮቶች የተነሳ ከመደበኛው የትምህርት ስርአት መገለል እንደሌለባቸው ፣ እንደዚሁም የቅድመ መደበኛ ፣ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች እና የከፍተኛ ትምህርት እርከኖች ፣ ለእነዚህ ወገኖች የአካቶን ትምህርት ጥራት ባለው አኳኋን ተደራሽ ማድረግ እንደሚገባቸው ተደንግጓል ። በተጨማሪም ፣ የሚቀርብላቸው ትምህርት ፣ የተማሪዎቹ ፍላጎትና ችሎታ ላይ ተመርኩዞ መሆን እንዳለበት ሲገለጽ፣ አለፍ ብሎም ተማሪዎቹ ውጤታማና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ፣ በዘላቂነት ልዩ ድጋፍ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል ፤ ከዚህም ሌላ ፣ የተነደፉቱን የአካቶ ትምህርት ግቦች ስኬታማ እንዲሆኑ የተማሪዎቹ ማህበራዊ እና ቁሳዊ አካባቢ ፣ በትምህርት አቀባበላቸው እና በማህበራዊ እድገታቸው ገንቢ መሻሻል እንዲኖራቸው በሚያስችል ሁኔታ መደራጀት ብሎም መቅረብ እንደሚኖርበት ተመልክቷል Mistry of Education(1994)።

## 2.2. የአካቶ ትምህርት አጀማመር

ሰዎች በተለያዩ የህይወት ውጣ ውረድ ሲኖር ፣ ስኬትማ ሊሆን ፣ አልያም ደግሞ ዉጤቱ የተገላቢጦሽ ይሆናል፤ በዚህ መሐልም ከቀላል እስከ ከባድ ለሚደርስ አካላዊ ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ስነልቦናዊና መሰል ቀውሶች ሲጋለጡ፣ በተጨማሪም በእነዚህ አሉታዊ ሁኔታዎች የተነሳ በማህበረሰቡ ዘንድ የተሳሳተ አመለካከት እያደረ ፣ ለብዙ ዘመናት እነዚህ ወገኖች የመብቶቻቸው ተጠቃሚ ሳይሆን ቀርተው፣ ከዚህ በከፋ መልኩ የሌሎች ዋነኛ ሆነው መቅረታቸውን ትምህርት ሚኒስቴር  ጠቁመዋል። በተጨማሪም ፣ በቆዳ ቀለም ፣ በፆታ ልዩነት ፣በዘር ፣ በሃይማኖት፣ በባህል እና ተያያዥ ጉዳዮች የተነሳ ፣ ሰዎች መገለልና መድልዎ ሲደርስባቸው፣ ማህበረሰቡም መሰል ገንቢ ያልሆነ ግንዛቤና አመለካከት መያዙን ዓለማየሁ (2016) ገልፀዋል።

አካል ጉዳተኞች ፣ ወላጅ አልባዎች፣ በኑሮ ደረጃ የአእምሮ ዘገምተኛኞች እና የመሰል ችግር ሰለባዎች ፣ ለማህበረሰቡ የሚያገኙት አፀፋዊ ምላሽ አበረታች ባለመሆኑ፣ ልዩ ልዩ መብቶች እንደዚሁም አቅርቦቶች ተደራሽ እንዳይሆኑላቸው ሲስተዋል ፣ ለአብነትም የትምህርት ግልጋሎት ተጠቃሚ አለመሆናቸው ይጠቀሳል (Meseret ;2004)። በኋላም ቀስ በቀስ በተደረጉ የፖሊሲ ማሻሻያዎችና ጥናቶች መሰረትነት፣ የተለያዩ ችግር ላለባቸው ህፃናትና ወጣቶች ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥባቸው ስፍራዎች በውስን ቁጥር ተደራጅተው ስራ ሲሰሩቆይቷል ፤ በተያያዘም፣ በቅድሚያ እነዚህ የተገላሉ የእውቀትና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከላት ወይንም የአዳሪ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ሲሰጡ ከቆዩ በኃላ፣ በሂደትም በተሰሩ ጥናቶችና ግምገማዎች፣ የትምህርት ስፍራዎቹ ያስገኙት ፋይዳ ተጨባጭ እንዳልሆነ ተደርሶበት ህፃናቱና ወጣቶቹ በመደበኛ የትምህርትና የስልጠና ማዕከላት በልዩ ክፍሎች ችግር ያለባቸውና ሌሎች ተማሪዎች ተቀናጅተው የሚማሩበት አውድ ተፈጥሮና

የፖሊሲ ማሻሻያ ተደርጎ ለተወሰኑ አስርት ዓመታት የመማር ማስተማሩ ስራ ቀጥሎ ነበር (ዓለማየሁ ተ/ማሪያም፥2016) ። ይሁን እንጂ ፣ በቅንጅት የመማሩ ክንውን የተሟላ እንዳይሆን ተግዳሮቶች ሲስተዋሉበት ፣ ዋናው የማስተማሪያ ክፍሎች በሁሉም የትምህርት ማዕከላት የማይገኙ እና በተመረጡ ውስን ስፍራዎች ከመሆናቸው የተነሳ ፣ ማንኛውም አካል ጉዳተኛ እንደዚሁም ሌሎች የመማር ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ከቤተሰቡ ጋር እየኖረ ቅርቡ ባለ ትምህርት ቤት ተካቶ የመማር መብቱ ተገድቧል፤ ከዚህ የተነሳ ፣ እነዚህ ወገኖች አጠገባቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች የእውቀት ብሎም የክህሎት ድጋፍ የማግኘት መብት እንዳይኖረው ሆኗል ፤ በመሆኑም ፣ ይህ አሳሳቢ ጉዳይ ለረጅም ጊዜያት ጥናትና ምርምር ሲከወንበት ቆይቶ ፣ በ1978 እ.ኤ.አ በአካቶ ማስተማር ወይም የአካቶ ትምህርት (Inclusive Education) የሚል ጽንሰ ሐሳብ በእንግሊዝ ብቅ ሲል እንደቻለ አመልክተዋል።

በአሜሪካን ሀገርም በ1980ዎች መጨረሻ አካባቢ የአካቶ ትምህርት ተሟጋቾች የአካል ጉዳተኞችና የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ፣ ሰነልቦናዊ፣ አእመሯዊ ችግር ለህግ ያለባቸው፣ እንደዚሁም ሌሎች ተማሪዎች ግብ ያለው ጥምረት ፈጥረው በመደበኛ ትምህርት ቤትና ክፍሎች መማር እንደሚገባቸው ሲቀሰቅሱና ማህበረሰቡን ሲያነቁ ቆየተው ፣ በ1990ዎቹ ዓመታት ቀጥሎም በአዲሱ ሚሊኒየማቸው ፣ የአካቶ ትምህርት ተደራሽነት ብሎም ትግበራ የበለጠ ሊስፋፉ እንደቻለ Lipsky እና Gartner (1997) ገልፀዋል ። በተያያዥነትም ፣ የተለያዩ ተጨባጭ የሆኑ የአካቶ ትምህርት እና ችግር ያለባቸው ህፃናት የተመለከቱ ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ፣ እያንዳንዱ ሀገር ይህን አዲስና ገንቢ የትምህርት አሰጣጥ ፍልስፍናን በተቻለ ፍጥነት በትምህርት ስርዓታቸውና በህግ ማዕቀፎቻቸው ውስጥ አካተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ መወሰኑ ፤ የአካቶን ትምህርት በየአህጉራቱ በሚገኙ ሀገራት እንዲጀመር አቅም መፍጠሩን ተጠቁሟል ( UNESCO : 1994) ።

በተጓዳኝም የኢትዮጵያን የአካቶን ትምህርት ጅማሬ ሲታይ ፣ የክርስትና ሀይማኖት ከመተዋወቁና ከመስፋፋቱ ጋር ቁርኝት ያለው ሲሆን ፣ በቤተ ክርስቲያን የመሳፍንት ልጆችን ፣ ተሰጥኦና ችሎታ የታደሉትን በተጨማሪም ሌሎች ክህሎት ያላቸውን ህፃናት አብሮ በማስተባበርና በማብቃት የተደረገው ጉልህ ጥረት ፣ በአካቶ ማቆጥቆጥ ሚና እንደ ነበረው ። እና በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተበረከተው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነበር (Zelaleew Temesegen : 2014) ።

በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት ታሪክ ፣ አካል ጉዳተኞች ብሎም ሴቶች ልጆችን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ለማስረፅና ሊቃውንቶችን ለማፍራት በሰፊው ጥረት ሲደረግ ፣ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ማለትም 1520 ኢትዮጵያን የጎበኘው ፍራንሲስኮ አልፌሬዝ ፣ የጉዳዩን ተጨባጭነት ህቅ መሆኑን ምስክርነቱን ሰጥቷል ። ይህ የውጭ ሀገር ዜጋ በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ሲገለጽ ፣ አካላዊ ጉዳት ያጋጠማቸው ፣ የማየት ችግር ያለባቸው ፣

እንደዚሁም ተሰጥኦና ችሎታ የታደሉ ችግር ያለባቸው ፣ እንደዚሁም ተሰጥኦና ችሎታ የታደሉ ልጆች በህብረት ሲማሩ እንደነበረ ፣ በተጨማሪም ከመካከላቸውም በትምህርታቸው የላቁት ፣ በቤተ ክርስቲያኒቷ የክህነትና የሊቃውንት የላቀ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን Zelalem Temlsegen (2014) ጠቁመዋል ።

## 2.3. የአካቶ ትምህርት በዓለምና በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የህግ ማዕቀፍ

የአካቶ ትምህርት የህግ ይሁንታ በማግኘት እንደ ተግባር ፣ በዓለም አቀፍ የመንግስት ድርጅት ብሎም በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች እንደዚሁም የትምህርት ነክ ጉዳዮች ውስጥ የህግ ከለላ ተበጅቶለታል። ዩኔስኮ 1994

ከ1948 ዓ.ም እንደ ጎርጎሳያን አቆጣጠር በፀደቀው አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋት ውስጥ በአንቀፅ 26 ለመጀመሪያ ጊዜ ማንኛውም ግለሰብ የትምህርት ግልጋሎት ማግኘት እንዳለበትና ትምህርት በነፃ ለሁሉም ህፃነት ቢያንስ በአንደኛ ደረጃ እርከን መዳረስ እንደሚያስፈልገው ይደነግጋል ፤ በአጠቃላይም ፣ ሰዎች እንደፍላጎታቸውና እንደ ችሎታቸው በጥራት መማር እንደሚገባቸው ተጠቅሷል (ትምህርት ሚኒስቴር፡ 2016)።

የ1966ቱ ዓለም አቀፍ የሶሻልና የባህል ስምምነት ትምህርት አለም አቀፍ መብት በመሆኑ ፣ የትኛውም የማኅበረሰብ አባል እንደዚሁም የየቱንም ባህል ተከታይ ሰው ፣ በተገቢው የትምህርት ግልጋሎት ሊያገኝ እንደሚገባው ተገልጻል። ከዚህ በተጨማሪም ፣ የ1975ቱ የአካል ጉዳተኞች መብቶች እንደሚጠቁመው ፣ የእነዚህን ወገኖች ችሎታ እንደዚሁም አቅም ለማዳበር ብሎም ማህበራዊ ግንኙነታቸውን የተሻለ ለማድረግ ፣ ዓለምና ሀገር ዓቀፍ ተግባራት መስራት እንዳለባቸው ሲገለፅ ፣በሚጠቀሙት የድጋፍም ይሁን የአገልግሎት አቅርቦት ላይ ሙሉ መብት እንዲኖራቸውም መደረግ እንደሚገባው ስምምነት ላይ ተደርሷል ( World Vision 2007)። ከተነሱት ጉዳዮች ጋር በተገናኘም ፣ የ1989ኙ የልጆችን መብት በተመለከተ የሚደነግገው ዓለም አቀፍ ስምምነት ሲገለፅ ፣ መሰረታዊ ነፃ ትምህርት እና አጥጋቢ ግልጋሎት ፣የስራ ዕድል የሚያስገኝ ጥራት የተላበሰ የመማር አውድ እና የተዝናኖት ዕድላቸውን የሚያሰፉ ዕድል ሊፈጠርላቸው ያስፈልጋል ፣ የአካል ጉዳት ላገጠማቸው እና ሌሎች የመማር ችግሮች ላሉባቸው ልጆች ደግሞ ከአካባቢያቸው ጋር የሚያደርጉትን ሁለንተናዊ እንቅሳቃሴ የሚያጎለብት ብሎም አጠቃላይ ስብዕናቸዎች ሊፈጠ ሩባቸው እንደሚያስፈልግ የተመለከተ ብቻም ሳይሆን ፣ ከቀደሙት ስምምነት በተሻለ ይኸኛው ልጆችን በብዙ መልኩ ሊጠቅሙ የሚያስችሉ ዝርዝር ህግጋት ማቀፉን ትምህርት ሚኒስቴር (2016) ።

በተመሳሳዪ መልኩም ፣ በጆሚተን ፣ በ1990 እንደ ጎርጎረሳውያን ዘመን ስሌት የአለም ትምህርት ለሁሉም ስብሰባ እገዳ ሲያስገነዘበው ፣ የአንደኛ ደረጃን የትምህርት እርከን አገልግሎት ማግኘት የልጆች ሰብዓዊ መብት መሆኑና ፍትሃዊ የትምህረት አቅርቦት

ማግኘት እንዳለባቸው አካል ጉዳተኞች ጨምሮ መጠቆሙ ፣ ሲገለጽ ፣ በ1993 በዚሁ ሰፍራ በተደረገው ኮንፍረስ ፣ የአካል ጉዳተኞ ልጆች እኩል የትምህርት እድል እንደ ሚያስፈልጋቸው መከሯል unesco (1994)፡፡ ልጆችንና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ ዓለም ዓቀፍ አጀንዳዎች እየጎለመሱ ሄደው በ1994 ይበልጥ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ተደረሰ ፤ በሰላምካ እስፓኝ ውስጥ የተካሄደው የዓለም ሀገራት ሰብሰባ ዋና የውይይት አጀንዳ የነበረውና ከስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ ፣ ማንኛውም ልጅ የራሱ የሆነ ልዩ በህርይ ፣ ፍላጎት ፣ ችሎታ እንደዚሁም የመማር አካሄድ ስላልው ፣ « በልዩ ፍላጎት ለሚታቀፉ ልጆች / ተማሪዎች በመደበኛ ትምህርት ቤት ፍላጎታቸውንና ችሎታቸውን ያማከለ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ መተግበር የግድ ያስፈልጋል » የሚል ውሳኔ ተላልፏል ፤ በጉባኤው በተጨማሪነትም ፣ የየትኛውም ሀገር የትምህርት ስርአት አይነተ ብዙ የሆኑትን የማህበረሰብ አይነት ባህርያት ብሎም ችግሮች በሚገባ ታሳቢ ማድረግ እንደሚኖርበት ፣ እንደዚሁም የአድልዎ አመለካከቶችን በማስወገድ ፣ ሁሉንም ማህበረሰብ የሚገዛ መልካም አሰራሮችን የሚያሰርፅ ፣ በአጠቃላይም የትምህርትን አቅርቦትን ለሁሉም ተደራሽ የሚየደርግ፡፡ ተጨባጭ አቅጣጫዎች ሊኖሩት ያስፈልጋል ( UNESO 1994)፡፡ ከ2000 እስከ 2006 ድረስ ባሉት ዓመታት እንደ ጎርጎርሳውያን አቆጣጠር ፣የአካል ጉዳተኞችን መብቶች የተመለከቱ ጉባኤች ሲካሄዱ ፣ በ200 የአለም የትምህርት ፎርም በዳካር ፣ በ2003 ሚሊኔም ስምምነት እና የ2006 የተባበሩት መንግስታት ስምምነት ፣አካል ጉዳተኞችን የመብቶቻቸው ተጠቃሚ በማድረግና በማብቃት ላይ ያተኮሩ እንደሆኑ ተመለላክቷል UNESCO; 2003፤፤

የሰላማንካ አዋጅና ትምህርት ለሁሉም ዜጎች (Education for All) የሚለው መርህ በብዛት የሚተገበረው በመንግስት ስር ሲሆን ብዙዎቹ መንግስታት ትምህርት ለሁሉም ዜጎች የሚለውን ግብ የሚያስፈፅሙት ከሃገራዊ ፖሊሲ አንፃር ነው፣ ነገር ግን በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ አካል ጉዳተኞችን በትምህርት ውስጥ እንዲሳተፉ ከማነሳሳት፣ ከመደገፍና የተለያዩ አቅርቦቶችን ከማቅረብ አኳያ ውስንነት አለ፡፡ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች የሚለው መርህ ግቡ በአካል ጉዳተኞች ብቻ ሳይሆን በሴት ተማሪዎችስ፣ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ጉሳዎችና ተገልለው በሚኖሩ ልጆች ሁሉ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

የአካቶ ትምህርት የማስተር ዕቅድ የወደፊት ራዕይ በኢትዮጲያ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ደጋፊ የሌላቸውና የመማር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የተለያዩ ጎሳ፣ ቋንቋና ፆታ ያላቸውን ሁሉ ማሳተፍ ነው፤፤ የመንግስት ፍላጎትም በኢትዮጲያ የትምህርት ስርዓት ውስጥ እኩልነትና ፍትሃዊነት ነግሶ ማየት ነው፡፡ ሁሉም ሕፃናትና ተማሪዎች እንደ ፍላጎታቸው ድጋፍ አግኝተው መማር እንዲችሉና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ፖሊሲው ይደግፋል Minister of Education (2016)፡፡

World Vision (2007) እንደገለፀው በኢትዮጲያ እስካሁን ድረስ ለአካል ጉዳተኞች ያለግንዛቤ በባህላዊ እይታ የተተበተበ፣ መገለልና መድሎ የጎላበት እንዲሁም ሰብዓዊነት ያልተላበሰና ቅጣት የተሞላበት ነው፡፡ በመሆኑም ጥሩሰው (2006) እንደገለፁት አካል ጉዳተኞችንና የመማር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የሚያስተናግዱ ታላሚ ትምህርት ቤቶች ብዙውን ጊዜ የተማሪዎን ፍላጎት ከመለየትና ከመደገፍ አኳያ ችግሮች ይታያሉ፡፡ Minister of Education (2004) እንደሚያብራራው በ1998ቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሃ ግብር ስትራቴጂያዊ አተገባበር ላይ ከተነሱ ድከመቶች አንዱ የግንዛቤ ውስንነት ነው፡፡ በአካል ጉዳተኝነት ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር የተደረገው ጥረት ውስጥ በመሆኑ አሁንም ቢሆን በሁሉም የትምህርት እርከኖች፣ በባለ ድርሻ አካላትና በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ አሉታዊ አመለካከት በስፋት ይሰተዋላል፡፡ በዚህ ምክንያት አብዛኞቹ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች አካል ጉዳተኛ ህፃናትን ለመቀበልና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ፍቃደኛ አይደሉም፡፡ሌላው የስርዓተ ትምህርቱ ተለማጭ አለመሆን ተጠቃሽ ድክመት ነው፡፡ ይህም ሲባል መምህራን መደበኛውን ስርዓተ ትምህርት ለእያንዳዱ ተማሪ እንደ የፍላጎታቸው ለማስማማት በሚያስችለቸው ስልጠና አልሰለጠኑም፡፡ በትምህርት ቤት ደረጃም ስርዓተ ትምህርቱን ለማስማማት የሚስችል የአተገባበር መመሪያ የለም፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ምክንያቶች ትምህርቱ ለአብዛኛዎቹ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ አይደለም ፡፡

በሰላማንካ አዋጅ የአካቶ ትምህርት መርሆች፣ ፖሊሲዎችና ትግበራዎችን በተመለከተ ከ300 በላይ ተሳታፊዎች፣ 92 የመንግስት ተወካዮችና 25 አለም እቀፋዊ ተቋማት ሰኔ 1994 ስምምነት ፈጥረዋል፡፡ ይህን ስምምነት የተባበሩት መንግስታት የህፃናት መብትም አፅድቋል፡፡ አዋጁ የመደበኛውን የትምህርት ቤት ፖሊሲና አተገባበር ከአካቶ ትምህርት ጋር እንዴት ተዛምዶ መቅረብ እንዳለበት በማዕቀፋዊ ስራ አሳይቷል (Unisco 1994)፡፡

በተባበሩት መንግስታት አጠቃላይ ስብሰባ ላይ የተሳተፉ 187 አገራት ስምምነቱን በማፅደቅ ስለአካል ጉዳተኞች የነበራቸውን ባህላዊ እይታ በፍጥነት እንዲለውጥ ተስማምተውበታል (Unisco 1994)፡፡ Pitres (2004) እንደጠቆሙት በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ድንጋጌ (1989) መሰረት ሁሉም ሕፃናት በማንኛውም ሁኔታ ሳይገለሉ በነፃነት የመማር መብት አላቸው፡፡ በተመሳሳይ Unisco (1994) እንደገለፀው በሰላማንካ ስምምነት አንቀፅ 28 ማንኛውም ሕፃናት ትምህርት የማግኘትና ዕድሎችን እኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸው ተረጋግጧል፡፡

Regmi (2017) እንደገለፀው በ1990ዎቹ ዓ.ም ትምህርት ለሁሉም ዜጎች በሚለው አለም አቀፋዊ አዋጅ መሰረት በትምህርት ላይ የነበረውን የግንዛቤ ክፍተት ለመሸፈን ተሞክሯል፡፡ ለአካቶ ትምህርት እድገት አስተዋፅኦ ከአበረከቱት መካከል አንዱ የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድልን የመጠቀም መብት 1993 ተጠቃሽ ነው፡፡ መብቱ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች ሁሉ ከአካል ጉዳተኛ አልባ ተማሪዎች ጋር ተካተው የመማር መብት እንዳላቸው ይገልፃል Pitres (2004)፡፡

## 2.4. ቋንቋና የአካቶ ትምህርት

የትኛዉም ቋንቋ ከሌላኛዉ አያንስም፤አይበልጥም፡፡ በተጨማሪም፣ የማንኛዉም ቋንቋ ባለቤት፤ በቋንቋዉ ባህሉን፤ እሴቱን ልምዱን ወዘተ ሊገልፅ፣ ለሌሎች ሊያካፍል፣ በአጠቃላይም ከሌሎች የማህበረሰብ አካላት ጋር መስተጋብር ሊፈጥር እንደሚችል ይገልፃል፡፡ ከዚህ የተነሳም፣ ተማሪዎች በቋንቋቸዉ የመጡበትን ቤተሰባዊና ማህበረሰባዊ ዳራ ሊያስተዋዉቁ፣ የአኗኗር ዘይቤን ሊያጋሩ ፣እምነትና ፍልስፍናዉን ሊያመላክቱ የሚችሉበትና የመሳሰሉት የመማሪያ አዉዶች የሚፍጥርላቸዉን እድሎች ማመቻቸት ይገባል ( Asrat D 2013)፡፡

አካቶ የትምህርት አሰጣጥም፣ ከላይ ከተነሱት የተማሪዎች ቋንቋ ልዩነት ጉደዮችን እንደ መሰረታዊ ግብዓቶች ተወስደዉ ተስማሚ የመማር ማስተማር፣ ብሎም የትምህርት ቤት ሁኔታን እንደሚፈጥር ሲራዳ፣ ተማሪዎች እርስ በእርስ በጥሩ ስሜት ዉስጥ ሆነዉ የእያንዳንደቸዉን ቋንቋ እንዲያደንቁ፣ ከዚህም በላይ በአብሮነት ለመማማር በር ይከፍትላቸዋል ( Hana Yeshinegus :2005) :: በተጨማሪም አካቶ፣ ተማሪዎች ከእነሱ አካባቢ የማይነገር ቋንቋ ይዘው በመጡ የክፍል አጋራቸዉ አዲስ መጪ ተማሪ አማካይነት ቋንቋዉን ለመልመድ ከሚያደርጉት ጥረት በተጓዳኝ ፣የዛን ስፍራ ተፈጥሯዊና ሰዉ ሰራሽ እሴቶች ለመተዋወቅ፣ልማዳዊና ባህላዊ ክዋኔዎች ለመገንዘብ ፣ እንደዚሁም በዙሪያቸዉ ለሚኖሩት የማህበረሰብ ክፍሎች እርስ በርስ ያላቸዉ ልዩነትን በጥሩ ጎኑ እንዲመለከቱት የሚያግዛዉ ስነ ትምህርታዊ ፍልስፍና ነዉ ጥበቡ (1995)

አካቶ ትምህርት ተማሪዎች ከእንቅፋት ነፃ የሚሆኑበትን አውንታዊና ምቹ ማህበረዊ ና አከባቢን መፍጠር ነው፡፡ ማህበረዊና ቁሳዊ አከባቢን ተደረሽ ማድረገ ነው (አለማየሁ 2016)፡፡ ከዚህም አንፃር የቋንቋ ትምህርትና በአካቶ ትምህርት ለማስተማር ምንም ድምፅ የማይሰማን ተማሪ ክፍል አስቀምጠን ብቻ ለማስተማር ብንሞክር ፋይደ የለውም፡፡ ይህ ተማሪ የምልክት ቋንቋ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ መጠነኛ የመስማት እክል ካለ ደግሞ የመስሚያ መሳሪያ ማቅረብ ያስፈልጋል ፡፡ አለበለዚያ ማስተማር አይቻልም፡፡ ለዓይነ ስውረን

ደግሞ በእጅ የሚዳስሱና በጆሮ የሚደመጡ የትምህርት መማሪያ መሳሪያዎችን እንደ ብሬልና የእንቅስቃሴ መሳሪያዎችን ማቀነጀት ያስፈልጋል።

የንግግርና የቋንቋ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ደግሞ የንግግርና የቋንቋ ወጌሻ (therapist) ያስፈልጋል።

የአዕምሮ ውስንነት ላለባቸው ደግሞ ተግባቦትን አሳንሶ ደረጃ በደረጃ የሚስተማር ያስፈልጋል። አውቲስቲክ ለሆኑ ልጆች ደግሞ ቋንቋን ተግባቦትና ማህበረዊ ክህሎትን ማደበር ይጠይቃል።

እንግድህ ቋንቋ ትምህርትን በአካቶ ትምህርት ተገብሮ ለሚድረግ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ግብዓቶችና መሳሪያነት ወሰኝ ነው። (አለማየሁ 2016)

## 2.5. የመምህራን አካቶ ትምህርት ግንዛቤ

ግንዛቤ ጥልቀት ያለው ግላዊ ስሜት ሲሆን በህይወት ልምድና በባህላዊ ተፅዕኖ ሊመሰረት ይችላል። በመምህራን ግንዛቤ ላይ የቀደመ ልምድ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል Peters (2004)። እንደካሴ (2013) አገላለፅ ሰዎች ካላቸው እይታ ወይም እምነት ጋር በተያያዘ አሉታዊ ወይም አውንታዊ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይችላል። የመምህራን ግንዛቤ ለማስተማር ሂደት በጣም ወሳኝ ሲሆን አሉታዊ የሆነ ግንዛቤ መኖር በክፍል ውስጥ ላለው የማስተማር ተግባር አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲፈጠር ያደርጋል Gal,Schoreur & Enger-yeger (2010)። Debore,pijil & Minnaer (2011) እንደገለፁት የአካቶ ትምህርት አተገባበር ስኬታማ ሊሆን የሚችለው መምህራን የአካቶ ትምህርት ሞዴልን ለመቀበል ዝግጁ ሲሆኑ ነው። በተመሳሳይ ተፈራ (1999) በጥናታቸው እንደገለፁት መምህራን ስለአካቶ ትምህርት አዎንታዊ ግንዛቤ ካላቸው የተማሪዎቸን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የትምህርት አሰጣጣቸውን እየለዋወጡ ተማሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲያደርጉ በአንፃሩ አሉታዊ ግንዛቤ ካላቸው ደግሞ በትምህርት አሰጣቸው ላይ ተማሪዎችን ሊጎዱና ሀላፊነታቸውን ሳይወጡ ሊቀሩ ይችላሉ።

መምህራን በትምህርት ሂደት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ አካላት ናቸው። በመሆኑም የመምህራን ክህሎት ቀስ በቀስ በማሳደግ ግንዛቤና አመለካከታቸውን መቀየር ይቻላል Slavico (2010)። እንደHattie (2009) ገለጻ የመምህራን ግንዛቤ በተማሪዎች የመማር ሁኔታ፣ በማስተማር ተግባርና በክፍሉ አጠቃላይ ገፅታ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል። Hay,smit & palusen (2002) እንደ ጠቀሱት አካቶ ትምህርት እንዳይተገበር ከሚያደርጉ ዋነኛ መሰናክሎች አንዱ የመምህራን ግንዛቤ ነው። መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ትግበራ

ብቁ የሆነ የስራ ላይ ስልጠና ባለመሰልጠናቸው መደበኛና ልዩ ፍላጎት ተማሪችን በማዋሃድ ልዩነታቸውን ታሳቢ አድርገው ለማስተማር እንዳይዘጋጁ አድርጓቸዋል፡፡

በተመሳሳይ Sharma, Forlin & Loroman (2008) እንደገለፁት መምህራን አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አካተው ለማስተማ ብቁ ዝግጅት አያደርጉም፡፡ ለዚህም ተጠቃሽ ምክንያቶች መምህራን በቂ ስልጠና አለመውሰዳቸው፣ ስርዓተ ትምህርቱን በጥልቀት አለማውቃቸውና በተማሪዎቹ መካከል ያሉ ልዩነቶችን አለመረዳታቸው ነው፡፡

Foriin, Jobling & Carroll (1999) እንደሚያስረዱት መምህራን ከልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ጋር ያላቸው የቀደመ ግንኙነት በግንዛቤያቸው ላይ ጥልቅ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በተደጋጋሚ ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚገናኙት በተወሰነ ጊዜ ከሚገናኙት አንፃር ሲታዩ ግንዛቤቸው የተሻለና አዎንታዊ ነው፡፡ በማለት ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

Hay, Smit & Palusen (2002) እንደጠቀሱት ከመምህራን ግንዛቤ ጋር ተዛማጅ የሆኑ በርካታ ተፅዕኖ አድራሽ ጉዳዮች አሉ፡፡ ለምሳሌ የአካል ጉዳተኞች አፈጣጠርና የትምህርቱ አቀራረብ ችግር በመምህራን ግንዛቤ ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱት ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንዲሁም በመምህራን ላይ ያሉ ተላውጦዎች ለምሳሌ ፆታ፣ ዕድሜ፣ የስራ ልምድ፣ የክፍል ደረጃ፣ ከአካል ጉዳኝነት ጋር ያለግንኙነትና ሌሎች ግለሰባዊ ምክንያቶች የአካቶ ትምህርት መርሆችን ለመቀበልና ለመተግበር ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡

Vygotsky (1993) እንደሚያብራው የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር የሚችል ከስራ በፊትና የስራ ላይ ስልጠና ነው፡፡ በመሆኑም ስለ አካቶ ትምህርትና ስለ ልዩ ፍላጎት ትምህርት ብዛት ያላቸውን የስራ ላይ ስልጠና የሰለጠኑ መምህራን በውስጣቸው አዎንታዊ ግንዛቤ እንዲፈጠርና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አካተው እንዲያስተምሩ ከፍተኛ እገዛ ያለው ሲሆን የስራ ላይ ስልጠና ማነስ ደግሞ በመምህራን ላይ ስለ አካቶ ትምህርት አሉታዊ ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ የስራ ላይ ስልጠና የመምህራንን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ ለማሻሻል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

እንደ Al-Katteeb (2002)ና Ben-Pajooh (1992) ገለጻ የስራ ላይ ስልጠና መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት አዎንታዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ወሳኝ ነው፡፡ ይህን ሃሳብ በመደገፍም Marchiensi (1998) እንደጠቆሙት የመምህራን ሙያዊ ስልጠና ለአካቶ ትምህርት አተገባበር ውጤታነት ቁልፍ ጉዳይ ነው በማለት ይገልጻል፡፡
ካሴ (2013) በእንግሊዘኛ ትምህርት የማየት ችግር (visual impairment)ያለባቸውን ተማሪዎች አካቶ መስተማር ላይ ባከናወኑት ጥናት እንዳመለከቱት መምህራን ስለአካቶ

ትምህርት ምንነትና ጠቀሜታ ያላቸው ግንዘቤ መካከለኛ የሚባል እንጂ ከፍተኛ ለማለት ማስደፍር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

Kern (2006) በመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ ላይ አድርገው ባካሄዱት ጥናት እንደጠቆሙት የመምህራንን ግንዛቤ ለመለካትና ለመለወጥ በጣም ከባድና አስቸጋሪ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

Hui (2015) በስኮትላንድ 6 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበርን መሰረት አድርገው ባጠኑት ጥናት እንዳሳዩት አብዛኞ መምህራን አዎንታዊ ግንዛቤ ያላቸውን የተሻለ አተገባበር የታየባቸው ናቸው፡፡ ለዚህ ውጤትም የመምህራኑ የማስተማር ልምድ ምክንያት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ካሴ (2013) በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት የማየት ችግር (Visual Impairment) ያለበቸውን ተማሪዎች አካቶ ማስተማር ላይ ባከናወኑት ጥናት እንዳመላከቱት መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት ምንነትና ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ መካከለኛ የሚባል እንጂ ከፍተኛ ለማለት የማስደፍር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የመምህራን ግንዛቤ በተማሪዎች የመማር ሁኔታ፣ በማስተማር ተግባርና በክፍሉ አጠቃላይ ገፅታ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል Hattie (2009)፡፡ እንደ Haw, Smit & Paulsen (2002) ገለፃ አካቶ ትምህርት እንዳይተገበር ከሚያደርጉ ዋነኛ መሰናክሎች አንዱ የመምህራን ግንዛቤ ነው፡፡ ይህን በመደገፍም ተፈራ (1999) እንደሚያስረዱት መምህራን ስለአካቶ ትምህርት አዎንታዊ ግንዛቤ ካላቸው የተማሪዎን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የትምህርት አሰጣቸውን እየለዋወጡ ተማሪዎች ተጠቃሚ ያደራጋሉ፡፡ በአንፃሩ አሉታዊ ግንዛቤ ካላቸው ደግሞ በትምህርት አሰጣጣቸው ላይ ተማሪዎችን ሊጎዱና ሀላፊነታቸውን ሳይወጡ ሊቀሩ ይችላሉ፡፡

የመምህራን ግንዛቤ ለማስተማር ሂደት በጣም ወሳኝ ሲሆን አሉታዊ የሆነ ግንዛቤ መኖር በክፍል ውስጥ ሳለው የማስተማ ተግባር አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲፈጠር ያደርጋል Gal, Engel & Yeggi (2010)፡፡

አካቶ ትምህርት በስፋት የሚመሰረተው መምህራን ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ባላቸው ግንዛቤ፣ በክፍል ውስጥ ላሉ ልዩነቶች ባላቸው እይታና ትምህርቱን ለመተግበር ባላቸው ሁኔታ ላይ ነው አውሮፓውያን ኤጀንሲ፣ (2003)፡፡ እንደ Gal,Engel & Yeggi 2010) ገለፃ በመምህራን ግንዛቤ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የማስተማር ልምድ፣ ዕውቀት፣ ከአካል ጉዳተኞች ጋር ያለ ግንኙነት፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶች አለመሟላትና የባህሪ ችግር ይጠቀሳሉ፡፡ አንድ ወይም በርካታ ምክንያቶች

ተደራርበው በመምህራን ግንዛቤ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ መምህራን የቀደመ የአካቶ ማስተማር ልምድ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ይህ ልምድ በፊት በነበራቸው ግንዛቤ የተነሳ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን ይችላል Jennifer (2015)፡፡

## 2.6. የመምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር

የአካቶ ትምህርት አተገባበር ስኬታማነት በመምህራን ግንዛቤ ብቻ ላይወሰን ይችላል Department of Education and skill (DES0),2010) ፡፡ አስራት (2013) በአካቶ ትምህርት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ አድራሽ ነገሮችን ለመለየት ባከናወኑት ጥናት እንደገለፁት ለአካቶ ትምህርት አተገባበር ስኬታማነት ወይም ውድቀት የመምህራን ስልጠና፣ የስርዓተ ትምህርቱ አረዳድ፣ የቁሳቁስ የመሟላት ሁኔታና የተለያዩ የገንዘብ ወጪዎች ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተለዩ የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ በአተገባበሩ ስኬታማነት ወይም ውድቀት ላይ ተፅዕኖ ያስድራል፡፡ ይህን ሃሳብ በመደገፍ እቴነሽ (2000) በኢትዮጲያ ሁኔታ ላይ ባናወኑት ጥናት እንደገለፁት አካቶ ትምህርት በተሳካ መንገድ እንዳይተገበር ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ የቁሳቁስ አለመሟላት ነው፡፡ በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይህን ችግር ለመቅረፍ በቀላሉ የሚዘጋጁ አካባቢያዊ ቁሳቁሶችን መምህራን ሲጠቀሙ አይስተዋልም፡፡

ጥሩሰው (2006) የኢትዮጵያ የአካቶ ትምህርት ዕድገትን መሰረት አድርገው ባጠኑት ጥናት በአካቶ ትምህርት ውስጥ የተለያዩ ስብጥሮችን ታሳቢ አድርጎ ለመተግበር ሂደቱ ቀላል የማይባል ጥረትን እንደሚጠይቅ ጠቅሰዋል፡፡

Jennefer (2015) እንደሚያስረዱት መምህራን በአካቶትምህርት ትግበራ ውስጥ ትልቁን ሚና የሚጫወቱ አካላት በመሆናቸው ለትምህርቱ ያላቸው ግንዛቤ ለአተገባበሩ ስኬታማነት ወሳኝ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ Mahony (2016) ይህን ሀሳብ በመደገፍ አካቶ ትምህርትን በተሳካ መንገድ ለመተግበር መምህራን በዕቅዳቸው ውስጥ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን መረጃ ለይቶ ማወቅ፣ የሚቀርበውን ትምህርት ለተማሪዎች በሚመች መልኩ ማደራጀትና ከልዩ ፍላጎት መምህራን ጋር ትብብራዊነትን መፍጠር የሚሉት ሊካተቱ ይገባል፤ ነገር ግን ስለአካቶ ትምህርት ስልጠና ያልሰለጠኑና የቀደመ ልምድ የሌላቸው መምህራን ይህን ለመተግበር ይቸግራቸዋል በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል፡፡

Hay, Smit & Pausen (2000) በደቡብ አፍሪካ የመምህራን የአካቶ ትምህርት ዝግጅትን በተመለከተ ባከናወኑት ጥናት እንደገለፁት መምህራን የመደበኛና የልዩ ፍላጎት ትምህርት

ተማሪዎችን በአንድ አካተው ለማስተማር አይዘጋጁም፡፡ ለዚ ዋነኛ ምክንያት ስለ አካቶ ትምህርት ትግበራዎች በቂ ስልጠና አለመውሰዳቸው ተጠቃሽ ነው፡፡

Alhassan (2014) በጋና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና ትግበራን በተመለከተ ባከናወኑት ጥናት እንደገለፁት መምህራን አውንታዊ ግንዛቤ ቢኖራቸውም ነገር ግን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ዕውቀታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

መምህራን ለአካቶት ትምህርት አተገባበር መሳካት ትልቁን ሚና የሚጫወቱ አካላት ናቸው፡፡ በመሆኑም ስለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ፣ ክህሎትና ፈቃደኝነት ትግበራው ውጤታማነት እንዲሆን ከፍተኛ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ Sharman (2013) ገለፃ የመምህራን የሙያ ዕድገት (professional Development) ለአካቶ ትምህርት ትግበራ ውጤታማነት አስተዋፅኦ አለው፡፡

Brakenriid (2011) ሲገልፁ አስፈላጊ የትምህርት ግብዓቶችን ማሟላት፣ ዕቅዶችን በጊዜ መመጠንና የተለያዩ ስልጠናዎን መሰልጠን ለአካቶ ትምህርት አተገባበር ስኬታማነት ትልቁን እገዛ ያበረክታሉ፡፡Slavica (2010) ይህን ሃሳብ በመደገፍ እንደሚያስረዱት ለአካቶ ትምህርት አተገባበር ከፍተኛ የሆነ ዝግጅትና ግልፅ የሆነ ራዕይ ሊኖር ይገባል፡፡ በተመሳሳይ Regmi (2017) ስኬታማ የአካቶ ትምህርት አተገባበር ውስብስብ ሂደቶችን እንደሚያካትት ገልፀዋል፡፡ ይህም ሁሉንም ልዩነቶችንና ማህበረ ባህላዊ ሁኔታዎችን ለመተግበር ግልፅ የሆነ ራዕይና ዝግጁነትን ይጠይቃል፡፡ Oliver (1996) እንደሚያብራሩት በትምህርት ስርዓት ውስጥ ለሁሉም ልዩነቶች ትኩረት መስጠት፣ ሁሉንም ተማሪዎች አካቶ ለማስተማር የሞራል ዝግጁነትን መፍጠርና ተለዋጭ ሆነ ስርዓት ትምህርት ሊኖር ይገባል፡፡

## 2.7. በመምህራን የአካቶ ትምህርት አመለካከትና ትግበራ ላይ አሉታዊ ሁኔታ የሚያሳድሩ ተፅዕኖዎች

አለማየሁ ተ/ማሪያም(2016) በአካቶ ትምህርት ዙሪያ በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ እንዳመለከቱት ፣ በአሁኑ የአለማችን የትምህርት ስርጭት ፣ የአካቶ ትምህርት ተግባራት በተገቢው እንዳይካሄድ ተግዳሮቶች ተንሰራፍተው ሲገኙ ፣ ለአብነትም ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናትና ወጣቶች ያለው ማህበራዊ አመለካከት አሉታዊ መሆን ፣የአካል ጉዳት ያላቸው ሰዎች በአካል ጉዳት የተገነባው ማንነታቸውን የድክመታቸው ሁሉ ብቸኛ ምንጭ አድርጎ ማየት ፣ ፈተናን ዋነኛ ማዕከል ያደረገ የትምህር ሥርዓት ፣ መምህራን ማዕከል ያደረገና መስተጋብራዊ ክንውኑ ያነሳ የማስተማሪያ ዘዴ ፣ የቁሳዊና የማህበራዊ አካባቢዎች ተስማሚ አለመሆን ፣ ለየተማሪው እንደ ፍላጎቱና ችሎታው ድጋፍ አለመኖር ፣ የወላጆች

በትምህርት ሂደት ተሳትፏቸው ማነስና ግልጽ ፖሊሲና የአፈጻጸም መመሪያዎች በየትምህርት ቤቱ አለመኖር ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው ::

የአካቶ ትምህርት ግብ የሚሳካው በትምህርት ማእከላት እንደዚሁም በቤት የአካቶን መርሆዎችን በእለት ተዕለት ከማከናወን አኳያ በሚተገብሩ ተጨባጭ ስራዎች ሲሆኑ ፣ ለውጤታማ የአካቶ መርህ ትግበራዎች ደግሞ በመምህራን ፣ ትምህርት አመራር ፣ በወላጆች ፣ በተማሪዎችና በማህበረሰብ ዘንድ የዳበረው እውቀት ፣ ክህሎት ፣ አመለካከትና ቁርጠኝነት ወሳኝ ድርሻ እንዳለው Michel (2005)ገልፀዋል :: ከእነዚህ ነጥቦች በመነሳት ፣ በመምህራን ዘንድ የአካቶ ትምህርት አመለካከትና ትግበራ ላይ አሉታዊ ጫና የሚያሳድሩትን ጉዳዮች መመልከት ተገቢ ይመስላል ::

መምህራን በአካቶ ትምህርት ሂደት የተፈለገውን ውጤት እንዳያመጡ የሚያደረጋቸው ጉዳዮች ሲኖሩ ፣ለአብነት ልምድ ፣የአካቶ እውቀት ፣የቀደመ ከአካል ጉዳተኞችና ከሌሎች ችግር ካለባቸው ተማሪዎች ጋር ያላቸው መስተጋብር ተሞክሮ፣ የአካል ጉዳተኞች የትምህርት መርጃና ቁሳቁስ ያለመሟላት፣ የአካል ጉዳተኞችና የመማር ችግር ያላቸው ተማሪዎች ውስን ባህርያትና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ ፤በሂደትም በተጠቀሱት ምክንያቶች፣ በአንዱ አልያም ከዚያ በላይ ሰበቦች ፣ አሉታዊ ግንዛቤ በመምህራን ዘንድ ይፈጠርና ፣ በኋላም ለአካቶ አሉታዊ አመለካከት በማሳደር ፣ በትምህርት የተነደፈው አላማ እንዳይሳካ ይደረጋል ጥሩሰው (2006) ::

በተጓዳኝ፣ ቀደም ሲል ከመምህራን የአካቶ ትምህርት አመለካከት ጋር ተያይዘው የተነሱት ጉዳዩች መሰረት በማድረግ ፣ የቋንቋ መምህራን ሁኔታ ምሁራን ለመቃኘት ሞክረዋል:

## ሀ) ወላጆችና ማህበረሰቡ

የመማር ማስተማር ሂደት ቁጥጥር እስከ የትምህርት ቤት ችግር መፍታት ደረስ በንቃት ተሳታፊ ናቸው :: ይሁን እንጂ ፣ በመማር ክንውን ውስጥ የአካቶን ትምህርት በተመለከተ ወላጆችና ማህበረሰቡ እያበረከቱ የሚገኙት ጥረት አነስተኛ እንደሆነ በተለያዩ በሀገራት ላይ ከጉዳዩ ዙሪያ የተሰናዱት ጥናቶች ይጠቁማሉ::

Mesrete ( 2004 ) እንዳመለከቱት ፣ ተማሪዎች የትምህርት አቅርቦትና ድጋፍ እንዲያገኙ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የወላጆችና የማህበረሰቡ ሚና ላቅ ያለ ቢሆንም፣ ለአካል ጉዳተኛ እና ስነ ልቦናዊ ቀውስ ላለባቸው ህጻናት / ልጆች ያዳበሩት የተዛባ አመለካካት፣ ሁሉም ህጻናት/ ልጆች በመተባበር የመማር ትግበራ የሚያከናውኑበትን የአካቶ የትምህርት አሰጣጥ እንዲጎለብት የሚያደርጉት ተነሳሽነትነትና ተሳትፎ ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል::

## ለ) የብቁ አመራር ችግር

በተለያዩ የአስተዳደር እርከን የሚገኙ መዋቅሮች ፣ ማለትም በፌደራል በክልል ፣ በዞን ፣በወረዳ ፣ በቀበሌ አልያም በክፍል ከተሞች ያሉ አመራሮች አይነታዊ አመለካከት ፣ እውቀትና ክህሎት በመያዝ ወደ ተጨባጭ ስራ መግባት የአካቶን የትምህርት ትግበራ ስኬታም እንደሚያደርገው ይገለፃል ፤ እነዚህ አካላት ዕቅድ ሲያዘጋጁና በጀት ሲመድቡ የልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ታሳቢ ማድረግ ሲጠበቅባቸው፣ በተለይ ደግሞ የትምህርት ቤት ርዕስ መምህራንና መምህራን ከሁሉ ቀድመው የአካቶ ትምህርት ባህልን በመገንባት የክትትልና የቁጥጥር ተግባር ማከናወን እንዳለባቸው ፣Meseret ( 2004 ) በጥናታዊ ፅሑፋቸው ጠቁመዋል ::ከተነሳው ሃሳብ ጋር በተጎዳኝም፣ የአካቶ ትምህርት በተገቢው እንዲተገበር እና የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ፣ የትምህርት ቤት አመራር በየዕለቱ ፣ በየሳምንቱ ፣ በየወሩና በየአመቱ ከትምህርት ቤት ባለ መራቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርባቸዋል ፤ ተማሪዎቻቸው እንደ ችሎታቸውና ፍላጎታቸው ተምረው አጥጋቢ ውጤት እንዲያመጡ መርዳት የሚጠበቅባቸው ሲሆን ፣ ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን መጠየቅ የሚገባቸው መሆኑን Fisher (2002) አመላክተዋል::

## መ). በትምህርት ቤቶች የመማሪያና የድጋፍ መሳሪያዎችና መስጫ አቅርቦቶች ችግር

UNESCO (2003) በአመታዊ ሪፖርቱ እንዳመለከተው ፣ እጅግ ብዙሃን በመሆኑ የትምህርት ማእከላት ለተማሪዎች የመማሪያ መሳሪያዎችና የድጋፍ መስጫ አቅርቦቶች የማነስና የተደራሽነት ችግር ሲስተዋል ፣ በተለይም ደግሞ ለአካል ጉዳተኞች እንደዚሁም ሌሎች ልዩነት ላላቸው ተማሪዎች ሁኔታው የከፋ ነው :: ድርጅቱ የታየውን አሉታዊ ጉዳይ ሲያብራራ ፣ የትምህርት መሰረተ ልማት በማየታይባቸው ፣ ይልቁንም ከከተሞች ዳር ያሉ እና ገጠርማ አካባቢዎች ፣ ሁሉን አቀፍ ትምህርት ለማዳረስ አስቸጋሪነቱ የጎላ ሲሆን ፣ ለዚህ ምክንያት የመማሪያ ክፍሎች ተማሪዎቹን ያማከሉ ሆነው ያለመገንዘባታቸው እንደሆነ ሲጠቁም ፣ ይህም በመልሱ ተማሪዎቹ ደህንነትና ምቾት እንዳይሰማቸው አድርጓቸዋል :: በመሆኑም ፣ አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች በአካቶ ትምህርት ትግበራ አመቺ እንዳይሆኑ በር ከፍቷል ::

የአካቶትምህርት አተገባበር ስኬታማነት በመምህራን ግንዛቤ ብቻ ላይወሰን ይችላል (Department of Education and skill (DES0),2010) :: አስራት (2013) በአካቶትምህርት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ አድራሽ ነገሮችን ለመለየት ባከናወኑት ጥናት እንደገለፁት ለአካቶትምህርት አተገባበር ስኬታማነት ወይም ውድቀት የመምህራን ስልጠና፣ የስርዓተ ትምህርቱ አረዳድ፣ የቁሳቁስ የመሟላት ሁኔታና የተለያዩ የገንዘብ ወጪዎች

ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተለየ የመምህራን የአካቶትምህርት ግንዛቤ በአተገባበሩ ስኬታማነት ወይም ውድቀት ላይ ተፅዕኖ ያሰድራል፡፡ ይህን ሃሳብ በመደገፍ እቴነሽ (2000) በኢትዮጲያ ሁኔታ ላይ ባከናወኑት ጥናት እንደገለፁት፣ አካቶ ትምህርት በተሳካ መንገድ እንዲተገበር ከማያደርጉ ነገሮች አንዱ የቁሳቁስ አለመሟላት ነው፡፡ በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይህን ችግር ለመቅረፍ በቀላሉ የሚዘጋጁ አካባቢያዊ ቁሳቁሶችን መምህራን ሲጠቀሙ አይስተዋልም፡፡

Jennifer (2015) እንደሚያስረዱት፣ መምህራን በአካቶ ትምህርት ትግበራ ውስጥ ትልቁን ሚና የሚጫወቱ አካላት በመሆናቸው ፣ ለትምህርቱ ያላቸው ግንዛቤ ለአተገባበሩ ስኬታማነት ወሳኝ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ Mahony (2016) ይህን ሀሳብ በመደገፍ ፣አካቶ ትምህርትን በተሳካ መንገድ ለመተግበር መምህራን በዕቅዳቸው ውስጥ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን መረጃ ለይቶ ማወቅ፣ የሚቀርበውን ትምህርት ለተማሪዎች በሚመች መልኩ ማደራጀትና ከልዩ ፍላጎት መምህራን ጋር ትብብራዊነትን መፍጠር የሚሉት ሊካተቱ ይገባል፤ ነገር ግን ስለአካቶ ትምህርት ስልጠና ያልሰለጠኑና የቀደመ ልምድ የሌላቸው መምህራን ይህን ለመተግበር ይቸግራቸዋል በማለት ሀሳባቸውን ገልፀዋል፡፡

## 2.8. በመምህራን አካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ የሚገጥሙ ተግዳሮቶች

መማርን ስኬታማ ለማድረግ ጥራት ያለው የትምህርት ቤት አካባቢን መፍጠር፣ ለአካቶ ተግባራዊነት ወሳኝ ጉዳይ ነው ካሴ 2013 ፡፡ ትምህርት ቤቶች በኢኮኖሚና በማህበራዊ ደረጃዎችው ልዩነት ካላቸው ወላጆች የሚመጡ ተማሪዎች የአካቶ ትምህርት መርሆች የመተግበር ኀላፊነት አለባቸው ተፈራ (1999) ፡፡ የተለያዩ የኑሮ ደረጃ፣ የባህል፣ የቋንቋና የፆታ ልዩነት ኖሯቸው፣ በመሀላቸው የመከባበር ባህል እንዲዳብርና እንዲተባበሩ ለማድረግ፣ ትምህርት እንዲዚሁም ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም፣ አወንታዊና ተነሳሽ የሆነ የክፍል ድባብን መፍጠር ተማሪዎች ገንቢ የተግባቦት ልምድ እንዲኖራችው፣ማህበራዊ ክህሎታቸውን ማሳደግ፣በመተባበር እየተማሩ አካቶን እውን እንዲያደርጉ ያግዛል፤ታደሰ 2013 ተማሪዎች እንዴት እንዳሚያስቡ በማስተባበር ፣ አሉታዊ አስተሳሰባቸውን እንዲቀይሩና የባህሪ ለውጥ እንዲመጣ ክትትል በማድረግ ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ፣ ተማሪዎች የተማሩትን ነገር የሚያስታውሱበትን ስልት ማሳየት ፣ ያነበቡትን እንዲረዱ ድጋፍ በማድረግ እንዲለማመዱ እድል በመስጠት ተጨባጭ ስራዎች ማከናወን ፣ ለአካቶ ብሎም ለትምህርት ጥራት መምጣት ሚናው የላቀ እንደሆነ ጥሩሰው ( 2006 ) አመላክተዋል ፡፡ከላይ ከተገለጸው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ፣አካቶ ትምህርት ማለት ልዩ ልዩ ፍላጎትና ችሎታ ያላቸውን እንደዚሁም ሁሉንም ተማሪዎች

ጨምሮ ፣ በመደበኛ ትምህርት ቤትና በመደበኛ ክፍል ውስጥ ፍላጎታቸው በሚፈለገው ደረጃ እንዲማሩ ማድረግ ሲሆን፣ ለዚህ ስኬት ደግሞ ስርአተ ትምህርቱ ፣የማስተማር ዘዴዎች ፣የተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ፣ የሚመርጡት የመማር ማስተማር አቀራረብ፣ የሚወስኑት የመማር መተግበሪያ የትምህርት ግብአቶችና የመሳሰሉትን በሚገባ መመቻቸት ይኖርባቸዋል (Dyson እና ሌሎች፣እንደዚሁም ጥሩሰው (2006)::

በተጓዳኝ ደግሞ፣ የመምህሩ/ሯ የትምህርትና የስልቦና ሁኔታ የአካቶን ወደ ማስልጠኛ አልያም ትምህርት ተቋማት ለመግባት ከሚዘጋጅበት ያለው የምልመላ ሂደት ጀምሮ እና ሌሎች ሁኔታዎች በተገቢው ሊፈተሹ እንደሚገባቸው ሲገለጽ፣ መሰል ጉዳዮች በአካቶ ትምህርት ትግበራ ላይ አሉታዊ ጫና ያሳድራሉ አለማየሁ (2016) :: በአካቶ ትምህርት ትግበራ ላይ ተግዳሮቶች ከሚያመጡት ነገሮች ፣የመጀመሪያው ነጥብ ተቋማት የሚከተሉት የምልመላ መስፈርት ነው፤ ከጅምሩ አሉታዊ ስብእና ያላቸውን ግለሰቦች በሚገባ ሳይመረምሩ ለትምህርትና ስልጠና በማስገባት ለስራ አለም እንደበቁ ይረዳል:: እነዚህ መምህራንም አካቶን ሲተገብሩ፣ ለተማሪዎች የሚገባቸውን እንደዚሁም የፍላጎታቸውን ያህል እንክብካቤ ስለማያደርጉላቸው ፣ ተፈላጊው ለውጥ እንደማይታይ ተጠቁሟል ጥሩሰው (2006) :: በተጨማሪም መሰል የመምህርነት ስብዕና ያልተላበሱ መምህራን፣ ተማሪዎችን ለማገዝና ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ ፍላጎቱና አቅሙ ስለሌላቸው፣ ሁሉንም ተማሪዎች በሚዛናዊነት ለሚያቅፈው የአካቶ ትግበራ ምቹ አይደሉም ካሴ (2016) ::

በተያያዘም፣ የመምህሩን የአካቶ ትግበራ ወቅት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድረው፣ ስርዓት ትምህርቱ ነው፤ ይህ የአንድ ሀገር ፍኖተ ትምህርት ሲሆን፤ በውስጡም የትምህርት፣ በርዕይ፣ እሴት፣ ተልዕኮ፣ ግብ፣ ዓላማ፣ ይዘት፣ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ፣የመማሪያ ግብአቶች፣ የምዘና ስልቶችንና የመሳሰሉተትን የያዘ ሰነድ ነው:: በዚህ የትምህርት ፕሮግራም፣ እንደ ተማሪዎቹ ዕድሜ፣ የክፍል ደረጃና ዳራ የየትምህርት ይዘቶችና ዓላማዎች ተከፋፍለው ይቀመጣሉ፤ ይሁን እንጂ ፣ በሀገራችንም ይሁን በልሎች ባለደጉ ሀገራት፣ ልዩ ፍላጎት ሆነ ተያያዥ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ታስቦ በተጨባጭ የቀረበ ስርዓት ትምህርት አልያም የስርዓት ትምህርት ክፍል እንደሌለ Greene ( 2017) አመልክተዋል:: በሌላ በኩል፣ ስርአት ትምህርቱን በተነፃፃሪነት የተለያዩ የመማር ችግር ለለሌባቸው ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ፣ ማየት ለተሳናቸው፣ በአካል ጉዳተኞች፣ የአእምሮ ዘገምተኞች፣ የማህበራዊና የስነልቦናዊ ቀውስ ለገጠማቸውና ለመሳሰሉት ችግሮች ሰለባ ለሆኑትም ጭምር እያስማሙ ማቅረብ ሲገባ፣ መምህራን እነዚህን ሁኔታዎች አመቻችቶ በመማር ማስተማሩ፣ ይልቁንም በአካቶ ትምህርት፣ የማስኬድ ተግዳሮት ታይቶባቸዋል ታደሰ (2013) :: በተያያዘም፣ በአብዛኛው መልኩ፣ ስርዓተ ትምህርት የተለያዩ ፍላጎትላላቸው ተማሪዎች የትምህርት ስኬት ዕድል ስለማይሰጥ፣ መምህራን በአካቶ ትምህርት የትግበራ ሂደት ልዩ

ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንዳይተገብሩና የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት እንዳያሟሉ የሚደረግ ሚናው ከፍተኛ በመሆኑ፣ ተማሪዎችም ተነሳሽነታቸው ብሎም ተሳትፏቸው አርኪ እንዳይሆን አድርጓል Alhassan (2014 ) :: ጥሩሰው ( 1999 ) sharmn ( 2013) ዋቢ በማድረግ እንደገለፁት፣ መምህራን ለአካቶ ትምህርት አተገባበር መሳካት ከፍተኛውን ድርሻ ያላቸው አካላት በመሆናቸው፣ ስለ አካቶ ትምህርት ያዳበሩት ግንዛቤ፣ ክህሎትና ፈቃደኝነት፣ ክንውኑ ተጨባጭ መሻሻልና ለውጥ እንዲሆን ተፅዕኖ ያሳድራል፤ ከዚህ አካያ፣ የመምህራን ሙያዊ እድገት ( Professional Development ) ለአካቶ ትምህርት ትግበራ ስኬታማናት ጉልህ ቦታ አለው:: በተጨማሪም፣ የአካቶ ትምህርት ትግበራ በተገቢው እንዳይሳካ ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል፣ መምህራን በቂ የስራ ላይ ስልጠና አለማግኘታቸው ተጠቃሽ አሉታዊ ሁኔታ እንደሆነ ሲጠቀስ፣ ይህ አሉታዊ ጉዳይ በመልሱ፣ መምህራን ልዩነት ያላቸውን ተማሪዎች ለመርዳት የሚተገብሩት የማስተማሪያ ዘዴ መረጣና አጠ ቃቀም፣ የትምህርት መረጃዎችና ድጋፎች አሰነዳድ፣እንደዚሁም የግምገማና የምዘና ስልቶች የማቀድ፣ የማዘጋጀትና የመተግበር እውቀታቸው፣ ክህሎታቸው ፣ብሎም ተሞክሯቸው ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል አስራት (2013 ) ::

European Agency ( 2003 ) እንዳስገነዘበው በአካቶ ትምህርት የመምህራን ሁለናተናዊ እንቅስቃሴ የሚጠይቅ ሲሆን፣በአቢይነት መምህራን አካላዊ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ባላቸው ምልከታ፣ ለሌሎች ልዩነቶች በሚሰጡት እይታ ብሎም የመማር ማስተማሩን ለመተግበር ዝግጁነት እንደሆነ በአፅንኦት ጠቁሟል:: በተጨማሪም በአካቶ የትግበራ ሂደት ፣የተለያዩ ልዩነቶቻችን የያዙ ልጆች የሚሳተፉ ሲሆን፣ የእነዚህን ተማሪዎች ባህርይና ችሎታ በመረዳት ተገቢውን ድጋፍ ለማበርከት ፣ከዚህ ባለፈም ያለባቸውን ችግሮች በመገንዘብ የመፈትሄ ለማመንጨትና ተጨባጭ ስራ ለማከናወን ፣ የመምህሩ አወንታዊ አመለካከት የማይተካ ሚና እንዳለው ትምህርት ሚኒስቴር ( 2004 ) ገልጸዋል::

Hui ( 2015 ) እንዳመላከቱት ፣ በራሳቸው የሚተማመኑትና ተነሳሽነት ያላቸው መምህራን ፣ በአካቶ ትግበራ ወቀት ዘርፈ ብዙ ልዩነት ይዘው ለሚማሩት ተማሪዎች ፣ፍላጎታቸውን ፣ አቅማቸውን ፣ድክመቶቻቸውን፣ በየዕለቱ በመከታተልንና በመለየት፣ የተጣጣመና ውጤት ተኮር የትምህረት አቅርቦት ለማከናወን ይጥራሉ:: በተቃራኒው ግን የብዙዎቹ ጥናቶች ግኝቶች የሚያስረዳው ፣ በአካቶ የትምህረት አሰጣጥ ፣ የመምህራን ተሞክሮ ተስፋ መቁረጥ ፣ ፍራቻ ያለው ፣ ብስጭት የተሞላው፣ እንደዚሁም በራስ መተማመን ያነሰው ሆኖ ሲገኝ ፣በጠቅላላው ግንዛቤያቸውና አመለካከታቸው ገንቢ እንዳልነበረ ተገልፃል ( Avramidis 2002):: በመሆኑም Meserte( 2004) እንዳስገነዘቡት፣ የመምህራን አወንታዊ ግንዛቤ ለመማር ማስተማር ሂደት ገንቢ ሚና ሲኖረው ፣በተቃራኒው ግን ከውጫዊው አልያም ከማህበራዊው አውድ አሉታዊ ግንዛቤ ካዳበሩ ፣ ምላሻቸው አሉታዊ አመለካከት ይሆንና ፣ተጨባጭ ውጤት ላይገኝ ይችላል::

## 2.9. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አካቶ ትምህርትን በተመለከተ ከተለያየ አቅጣጫ የውጭና የአገር ውስጥ አጥኝዎች ምርምር አከናውነዋል፡፡ ከሀገር ውስጥ ጥናቶች መካከል ጥሩሰው (2006) የኢትዮጵያ አካቶ ትምህርት እድገትን መሰረት አድርገው ባጠኑት ጥናት በአካቶ ትምህርት ውስጥ የተለያዩ ስብጥሮችን ታሳቢ አድርጎ ለመተግበር ሂደቱ ቀላል የማይባል ጥረትን እንደሚጠይቅ ጠቅሰዋል፡፡

የመምህራንን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ መሰረት በማድረግ ካሴ (2013) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት የማየት ችግር (visual inpailment ) ያለባቸውን ተማሪዎች አካቶ ማስተማር ላይ ባከናወኑት ጥናት እንዳመላከቱት መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ምንነትና ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ መካከለኛ የሚባል እንጅ ከፍተኛ ለማለት የማያስደፍር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተመሳሳይም ይህ ውጤት ታደሰ (2014) የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር መሰረት አድርገው ካጠኑት የጥናት ውጤት ተቀራራቢነት ታይቶበታል፡፡

በሌላ መልኩ አካቶ ትምህርትን በተመለከተ የተለያዩ የውጭ ጥናቶች ተከናውነዋል፡፡ Debore,Pijlil & Minnert (2011) የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤን መሰረት አድርገው በአካሄዱት ጥናት የአከቶ ትምህርት አተገባበር ስኬታማ ሊሆን የሚችለው መምህራን የአካቶ ትምህርት ሞዴልን ለመቀበል ዝግጁ ሲሆኑ ነው በማለት ጠቅሰዋል፡፡

Hay, Smit & Paulsen (2001) በጥናታቸው እንደጠቀሱት አካቶ ትምህርት እንዳይተገበር ከሚያደርጉ መሰናክሎች አንዱ የመምህራን ግንዛቤ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በመሆኑም መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ትግበራ ብቁ የሆነ የስራ ላይ ስልጠናዎችን ባለመሰልጠናቸው መደበኛና የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በማዋሀድ ልዩነታቸውን ታሳቢ አድርገው ለማስተማር እንዳይዘጋጁ እንዳደረጋቸው በጥናታቸው ገልፀዋል፡፡

Hui (2015) በስኮትላንድ በሚገኙ 6 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበርን ትኩረት አድርገው ባጠኑት ጥናት እንዳሳዩት አብዛኞች መምህራን አዎንታዊ ግንዛቤ ያላቸው ሲሆኑ እነዚህም የተሻለ አተገባበር የታየባቸው መሆኑን በጥናታቸው ጠቁመዋል፡፡

በሌላ መልኩ Alhassan (2014) በጋና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህረን የአካቶ ትምህርት ግንዛና አተገባበር በተመለከተ ባካሄዱት ጥናት እንደገለፁት መምህራን

አዎንታዊ ግንዛቤ ቢኖራቸውም ነገር ግን የአካቶ ትምህርት አተገባበር እውቀታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት አውንታዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና አተገባበራቸውም የተሳካ እንዲሆን ስልጠና ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን Al-Katteeb (2002) Ben- Pajooh (1992)ና Marchiesi (1998) በጥነታቸው ገልፀዋል፡፡

ይህ ጥናት መሰረት አድርጎ በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተካሄዱ አብዛኞች ጥናቶች የውጪ አገር ቢሆኑም በአገር ውስጥም አካቶ ትምህርትን ከተለያየ አቅጣጫ በመመለከት ምርምሮች ተከናውነዋል፡፡ ጥናቱ አንድም በአካቶ ትምህርት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከአገር ውስጥ ጥናቶች አንፃር ከተፈራ (1999)፣ ከጥሩ ሰው (2006) ና ከካሴ (2013) ጥናት ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በሌላ በኩል በመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከታደሰ (2014) ጥናት ጋር ይቀራረባል፡፡ ከውጭ አገር ጥናቶች ጋር ሲታይ ከKarn(2006)፣ ከAlhassan (2014) ና ከGreene (2017) ጥናት ጋር ይዛመዳል፡፡

በአጠቃላይ በመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር በሚመለከት በተመራማሪዎች መካከል የሃሳብ ልዩነት ታይቷል፡፡ በመሆኑም በመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ግምገማ ላይ ቁርጥ ያለ የውጤት ማሳያ አልተገኘም፡፡ ስለዚህም በዚህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ለመመርመር ተሞክሯል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## 3፡ የአጠናን ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ስልት

ይህ ጥናት የተጠናው በቅይጥ የአጠናን ዘዴ ሲሆን ንድፉም ገላጭ ነዉ፡፡ ስልቱ የተመረጠበት ምክንያት፣ የጥናቱ ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ምን እንደሚመስል በመመርመርና በመፈተሽ ላይ የሚያተኮር በመሆኑ ነው፡፡ ፣

### 3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች

ይህ ጥናት የተካሄደው በምስራቅ አርሲ ዞን ካሉት 102 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ5 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው፡፡ይህም የትምህርት ቤት ናሙና መረጣ አመቺ ንሞናን የናሙና መረጣ ዘዴ ነዉ፡፡ አጥኚዉ ዘዴዉን የመረጠበት ምክንያት፣ አጥኚው የመኖሪያ አከባቢና የስራ ቦታ  በናሙናነት ከተመረጡት ውስጥ አንደኛው ትምህርት ቤት የሚገኝበት ወረዳ ስለሆነና ቀሪዎቹ 4ቱ ትምህርት ቤቶች  አጥኚው ከሚገኝበት ወረዳ ተጎራባች ወረዳዎች ውስጥ  የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በመሆናቸው ለጥናቱ አመቺነት መልካም ነው ብሎ ስላመነ ነው ፡፡ እነዚህም ትምህርት ቤቶች አሚኛ ገስጋር ፣ በሌ ገስጋር ፣ ሴሩ አባስ ፣ሮቤ ዲደአ እና ዲክሲስ ናቸው፡፡የጥናቱ ተተኳሪዎችም በ2013 ዓ.ም በተጠቀሱት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ 66 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ ወንድ 25 ሴት 8 በድምሩ 33 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን  ናቸው፡፡ የመምህራን የናሙና አመራረጥ በቀላል እጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ነው ፡፡ አጥኚዉ ይህን የናሙና አመራረጥ ዘዴ የተጠቀመበት ምክንያት ለሁሉም መምራኖች እኩል እድል መስጠት አስፈላጊ ነው ተብሎ ስላመነ ነው፡፡

### 3.3. መረጃ መስብሰቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃዎች ለመሰብሰብ ግልጋሎት ላይ የዋሉት የመረጃ መስብሰቢያ መሳሪያዎች ሶስት ሲሆኑ፣እነሱም የፅሑፍ መጠይቅ ፣ ምልከታና ቃለመጠይቅ ናቸው፡፡

#### 3.3.1.የፅሑፍ መጠይቅ

ይህን ጥናት ለማጥናት ከሚወሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ የፅሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተመረጠበት ዋና ምክንያት ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር በፍተሻ ላይ ያተኮረ በስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የፅሁፍ መጠይቅ የመላሾችን ማንነት ስለማይጠይቅ መላሾች

አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ሊያበረታታቸው ከመቻሉም በላይ ለሁሉም ተጠኚዎች አንድ አይነት ጥያቄ ስለሚቀርብ ከጥያቄ አቀራረብ ልዩነት የተነሳ የሀሳብ ልዩነት እንዳይፈጥር የሚረዳና ከመረጃ አቀባዮች አንድ ወጥ ሆኖ በተፋጠነ መንገድ  መረጃ ለመሰበሰብ የሚግዝ መሳሪያ ነው ፡፡

ይህም የፅሁፍ መጠይቅ በመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላትኩረት ያደረጉ 24 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን ከቁጥር 1 እስከ 13 ያሉ ጥያቄዎች የመምህራንን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤን ይፈትሻሉ ፡፡ ከፅሁፍ መጠይቁ ከተራ ቁጥር 14 እስከ 24 የሉት ደግሞ የመምህራንን የአካቶ ትምህርት አተገባበርን መሰረት ያደረጉ ናቸው ፡፡ መጠይቆችም የተዘጋጁት የሊክርት ስኬልን መሰረት በማድረግ አራት አማራጮች የያዙ ናቸው ፡፡ እነዚህም  በጣም እስማማለሁ ፣ እስማማለሁ ፣ በጣም አልስማማምና አልስማማም የሚሉት  ሲሆኑ አማራጮቹ የተሰጡት የምዝገባ ነጥብ በጣም እስማማለሁ (4) እስማማለሁ (3) በጣም አልስማማም (2) እና አልስማማም (1) ነው ፡፡ መጠይቁ በናሙናነት ለተመረጡ 33ቱም ተሳታፊዎች የቀረበ ነው ፡፡ የፅሑፍ መጠይቁ ለዋናው ጥናት ከመቅረቡ በፊት ተገቢነቱና አስተማማኝነቱ ተፈትሿል ፡፡ በተጨማሪም በአጥኚው አማካሪና በዘርፉ ባለሙያዎች የታየ ነው፡፡

### 3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ

ለዚህ ጥናት ሌላው አስፈላጊ የሆነ መረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ ምልከታ ነው፡፡ ይህ የክፍል ውስጥ ምልከታ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበርን መሰረት ያደረጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተከናወነ ነው፡፡ ይህ የክፍል ምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሊመረጥ የቻልው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያለውን ተጨባጭ አተገባበር በቀጥታ የሚያሳይ በመሆኑ ነው ፡፡ በምልከታው የአካቶ ትምህርት አተገባበር የተመለከተ 10 ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን አዎ ወይም የለም የሚሉ አማራጭ መልሶችን ይዟል ፡፡

አጥኚው ምልከታውን ያከናወነው  መጋቢት 5/ 2013 እስከ ግንቦት 5/ 2013 ዓ.ም ሲሆን ÷በእነዚህ ቀናት ውስጥ በናሙናነት በተመረጡት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአንዱን የጥናቱን ተሳታፊ የአማርኛ ቋንቋ መምህር 10 የአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜዎችን በመጠቀም ነዉ፡፡በተጨማሪም አጥኚው ከጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል10 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ምልከታውን አከኗውኗል ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መረጣው በአላማ ተኮር ዘዴን በመጠቀም ነው ፡፡ አጥኚው ይህን ዘዴ የመረጠበት ምክንያት አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ ከሚል  ግምገማ በመነሳት ነው ፡፡ የክፍል  ምልከታው  የተከማወነው የመጀመሪያ ድግሪ ባላቸው በ5 ረዳት የክፍል ተመልካች  ነው ፡፡ የረዳት የክፍል ተመልካች

እንዲከወን የተደረገበት ምክንያት አስተማማኝና ሚዛናዊ መረጃ ለመሰብሰብ ከማሰብ የመነጨ ነው ። ለተጠኚዎቹና ለረዳት የክፍል ምልከታ ተግባሪዎች ለምልከታው ፈቃደኛ እንዲሆኑና በምልከታው ወቅት የተለየ ባህሪ እንዳያሳዩ ቀድሞ ስለጥናቱ አላማ አስገንዝቧል።

### 3.3.3. ቃለ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት ሌላው አስፈላጊ የሆነ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ መጠይቅ ነው ። ቃለ መጠይቁ የተከናወነው ከጥናቱ ተሳታፊ 10 የአማርኛ መምህራን ላይ ሲሆን÷ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መረጣው በአላማ ተኮር ዘዴን በመጠቀም ነው ። አጥኚው ይህን ዘዴ የመረጠበት ምክንያት አስፈላጊውን መረጃ ሳገኝባቸው እችላለሁ ከሚል ግምገማ በመነሳት ነው ። በዚህ ቃለ መጠየቅ የተሳተፉ መምህራን በክፍል ምልከታ ከተሳተፉት ውጪ ናቸው ። የቃለ መጠይቁ ጥያቄዎች ብዛት 6 ሲሆኑ 4ቱ መጠይቅ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቶ ትምህርትን ግንዛቤና አተገባበር የተመለከተ መረጃ ለማግኘት የቀረበ ነው። ቀሪዎቹ ቃለ መጠይቆች በአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ምን ምን እንደሆኑ መረጃ ለማግኘት የቀረቡ ናቸው ። አጥኚው ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተጠቀመበት ዋና አላማ÷የመምህራኑን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ለመፈተሸ ነው ። እንዲሁም ፣ ተሳታፊዎች ከሚሰጡት የመጠይቅ ምላሽ በተጨማሪ ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲናገሩ በማድረግ መረጃዎችን አሟልቶ ለመሰብሰብ ስለሚያግዝ ነው። የቃለ መጠይቁ አይነት ነፃ ቃለመጠይቅ ነው።

## 3.4. የጥናቱ ሂደት

የጥናቱ ዕቅድ ተገምግሞ ከፀደቀ በኋላ የሚከተሉትን ሂደቶች አልፏል። በመጀመሪያ የቃለ መጠየቅ የፅሁፍ መጠይቆችና የምልከታ የክፍል መቆጣተሪ ቅፅ ተገመገሙ። ከግምገማው የተሰጡ አስተያየቶችን መሰረት በማድረግ እስከ መጋቢት 1 ድረስ መጠይቆችና የክፍል መቆጣጠሪያ ቅፅ አስፈላጊውን ማስተካከያ ተደረገባቸው። ከመጋቢት 2 እስከ መጋቢት 12 2013 ዓ.ም ባሉት ቀናት ውስጥ አጥኚው የፅሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለመረጋገጥ ከጥናቱ ተሳታፊ ውጪ በሆኑ መምህራን ቅድመ ሙከራ አከናውኗል። የፅሁፍ መጠይቁ አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኋላም የጥናቱ ተሳተፊዎች ለመጠይቆች እና ለምልከታዎች ይተባበሩት ዘንድ አጥኚው በደብዳቤና በስልክ ሁኔታዎችን አስተካክሏል። ፍቃደኝነታቸውን ካገኘ በኋላ የአማርኛ ክፍለ ጊዜዎችን በመጠቀም በረዳት የክፍል ምልከታ መረጃ ሰብባቢዎች አማካይነት ምልከታዎችን አከናውኗል ። በመቀጠል የጽሁፍ መጠይቆችን በአካልና በደብዳቤ ለተሳታፊዎች እንደ ሁኔታው በማቅረብ ከተወሰኑ ሰአትና ቀናት በኋላ ሰብስቧል ።ቃለ

መጠይቁን ከተሳታፊዎች ሁኔታ አንፃር በኣካል አከናውኗል፡፡ በአጠቃላይ የጥናቱ መረጃዎች እስከ ከግንቦት 10 2012 ዓ.ም ተሰብስበዋል፡፡ ከእነዚህ ሂደቶች በኋላ አጥኚው መረጃዎችን የማጣራትና የማደራጀት ስራ አከናውኗል፡፡ በመጨረሻም መረጃዎችን እንደ ዓይነታቸው በመለየት መጠናዊና ዓይነታዊ በሆነ ዘዴ ተንትኗል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑት በገላጭ ስታስቲክስና በዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ነው፡፡እነዚህ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች የተመረጡበት ምክንያት በፅሑፍ መጠይቅ፣በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ከቃላት ትንታኔ በተጨማሪ  አሀዛዊ በሆነ መልኩ ተንትኖ ለማሳየት ነው፡፡

የጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መምህርን የተገኙ መረጃዎችን ለትንታኔ ከመቅረባቸው በፊት በትክክል ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ መሞላታቸው ተጣርቶ መረጃው ለትንተና በሚያመች መልክ ኮድ ተደርጎ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ላይ ሰፍሯል፡፡ በመጨረሻም ወደ ትንታኔ ከመግብቱ በፊት የመረጃ ማጣረት ስራ ተከናውኗል፡፡

በጥናቱ ውስጥ በፅሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች SPSS version 21 ሶፍትዌርን በመጠቀም ተተንትኗል ፡፡ይህም የፅሁፍ መጠይቅ መረጃዎች በነጠላ ናሙና ቲ -ቴስት (one Sampel t-test) እና ገለፃን በመጠቀም የተተነተኑ ሲሆን በምልከታ የተገኙ መረጃዎች በመቶኛ ስሌትና በገለፃ ተተንትነዋል፡፡እንዲሁም በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በገለፃ ብቻ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# 4፡ የውጤት ትንታናና ማብራሪያ


ይህ ጥናት የተካሄደው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ምን ያህል ግንዛቤ እንደላቸውና የአካቶ ትምህርት አተገባበራቸው ምን እንደሚመስል ለማወቅ ነው ። የጥናቱ ዓላማዎች ላይ በማመርኮዝ አስፈላጊ መረጃዎች በፅሑፍ መጠይቅ፤ በክፍል ውስጥ ምልከታና በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡ በኋላ ተተንትነዋል ። በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችም ከተዛማጅ ጥናቶች አንፃር ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል ። የጥናቱ ውጤቶችና ማብራሪያዎቻቸው ከዚህ በታች በሶስት ክፍሎች ቀርበዋል።

## 4.1. የተጠኚዎች ግለ-ማንነት

በዚህ ጥናት ለ33 መምህራን ፅሑፍ መጠይቅ ተበትኖ ሁሉም ስለተመለሰ የጥናቱ ምላሽ ስሌት 100 ፐርሰንት ሆነዋል። በጥናቱ ከታሳተፉ መምህራን መካከል 8 (24.2%) ሴቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ወንዶች ሲሆኑ ከተጣኚዎች መካከል አብዛኛዎቹ (66.7%) የመጀመሪያ ድግሪ ያጠናቀቁ ናቸው ። የታጣኚዎቹ አማካይ ዕድሜ 39.65 ዓመት ሲሆኑ ቀሪዎቹን የተጣኚዎች ግለ-ማንነት ሠንጠረዥ 4.1 ውስጥ መመልከት ይቻላል (ሠንጠረዥ 4.1)።

ሠንጠረዥ 4.1: የተጣኚዎች ግለ-ማንነት ዝርዝር

| ተቁ | ጥያቄ | አማራጭ | ምላሽ በ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ቁጥር | መቶኛ | Cum. |
| 1 | እድሜ | 20-30 ዓመት | 6 | 18.2 | 18.2 |
| | | 31-40 ዓመት | 11 | 33.3 | 51.5 |
| | | 41-50 ዓመት | 12 | 36.4 | 87.9 |
| | | 51-60 ዓመት | 4 | 12.1 | 100.0 |
| | | ድምር | 33 | 100.0 | |
| 2 | ፆታ | ሴት | 8 | 24.2 | 24.2 |
| | | ወንድ | 25 | 75.8 | 100.0 |
| | | ድምር | 33 | 100.0 | |
| 3 | የትምህርት ደረጃህ/ሽ | የመጀመሪያድግሪያላጠናቀቀ/ች | 5 | 15.2 | 15.2 |
| | | የመጀመሪያድግሪያጠናቀቀ/ች | 22 | 66.7 | 81.8 |
| | | ሁለተኛድግሪያላጠናቀቀ/ች | 3 | 9.1 | 90.9 |
| | | ሁለተኛድግሪያጠናቀቀ/ች | 3 | 9.1 | 100.0 |
| | | ድምር | 33 | 100.0 | |
| 4 | በመምህርነት ሙያ ላይ ያለህ/ሽ ቆይታ | 1-10 ዓመት | 10 | 30.3 | 30.3 |
| | | 11-20 ዓመት | 12 | 36.4 | 66.7 |
| | | 21-30 ዓመት | 8 | 24.2 | 90.9 |
| | | 31 ዓመትናከዚያበለይ | 3 | 9.1 | 100.0 |
| | | ድምር | 33 | 100.0 | |




ስዕል 4.1፡ የአማርኛ መምህራን የሥራ ልምድ በዓመት

ከዚህ ባላይ በስዕል 4.1 ላይ እንደተመለከተው አብዛኛዎቹ መምህራን ከ11 ዓመት እስከ 20 ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው ናቸው (ስዕል 4.1)።

## 4.2. የውጤት ትንተና

### 4.2.1 ከፅሁፍ መጠይቅ ግንዛቤና አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና

#### 4.2.1.1 ከፅሁፍ መጠይቅ ግንዛቤን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለቀረቡላቸው የተለያዩ የግንዛቤ ጥያቄዎች የሰጡት ምላሻች በሠንጠረዥ 4.2 ቀርቧል። ውጤቱም ከዚህ በታች ተገልፃል።

ሠንጠረዥ 4.2: የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለአካቶ ትምህርት ለቀረቡላቸው የግንዛቤ ጥያቄዎች የሰጡት መልሶች

| ጥያቄ | ብዛት | ስሌት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የመደበኛ ስሌት ልኬት |
| አካቶ ትምህርት የተማሪዎችን እኩልነት ለማስፈን የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ ነው፡፡ | 33 | 2.61 | 0.864 | 0.150 |
| አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከአካል ጉዳተኛ አልባ ተማሪዎች ጋር አካቶ ማስተማር ይቻላል | 33 | 2.12 | 0.992 | 0.173 |
| የአካቶ ትምህርት መርሃ ግብር ከልዩ ፍላጎት በተሻለ መልኩ መምህራንን እንዲዘጋጁ ይረዳል፡፡ | 33 | 2.79 | 0.820 | 0.143 |
| መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት እና ችሎታ ታሳቢ ማድረግ አለባቸው | 33 | 2.24 | 1.032 | 0.180 |
| መምህረን በአካቶ ትምህርት ውስጥ የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የበለጠ ሃለፊነት አለባቸው፡፡ | 33 | 3.09 | .947 | 0.165 |
| አካቶ ትምህርት በተማሪዎች መካከል የመገለል ሁኔታ እንዳይፈጠር ያደርጋል | 33 | 2.52 | 1.121 | 0.195 |
| በተለያዩ የቴክኖሎጂ ዉጤቶች (ኮንፒዉተር ፣ የድምፅ መሳሪያዎች----ወዘተ) እገዛ የአካቶ ትምህርት በትምህርት ቤትህ/ሽ ይሰጣል | 33 | 2.48 | 1.004 | 0.175 |
| መምህራን አካቶ ትምህርትን ለመተግበር ልዩ የስራ ላይ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡ | 33 | 2.42 | 1.001 | 0.174 |
| በአካቶ ትምህርት ትግባራ ሂደት የሚታዩ ችግሮችን ለመለየት ችግር ፈች ጥናት ማድረግ አዎንታዊ ለውጥ ያመጣል | 33 | 2.94 | 0.659 | 0.115 |
| የትምህርት ቤትህ/ሽ አስተዳዳር ለአካቶ ትምህርት ክንውን ተጨባጭ ድጋፍ (በቁሳቁስ ፣ በገንዘብ ፣ በክህሎት) ያደርጋል | 33 | 2.09 | 0.947 | 0.165 |
| ከማህበረሰብ ጋር ቁርኘት ፈጥረህ/ሽ በአካቶ ትምህርት ዙሪያ ተገቢ መሻሻሎችን የሚስተዋሉበት አዉድ አድብረሀል/ሻል | 33 | 2.06 | 0.864 | 0.150 |
| ተማሪዎችን አካቶ ማስተማር ለማህበራዊ ህይወታቸው ትልቅ ፈይዳ አለው፡፡ | 33 | 2.94 | 0.704 | 0.123 |
| በአካባቢህ/ሽ ያሉ መንግስታዊና መግስታዊ ያልሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ለአካቶ ትምህርት ተግባር ድርሻቸዉ ብዙም አይደለም | 33 | 2.03 | 0.951 | 0.166 |

በሠንጠረዥ 4.2 ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው አካቶ ትምህርት የተማሪዎችን እኩልነት ለማስፈን የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ ነው፤ ለሚለው ጥያቄ የመምህራኑ አማካይ ውጤት 2.61 ስለሆነ መምህራኑ ስለአካቶ ትምህርት የተማሪዎችን እኩልነት ለማስፈን የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ መሆኑን ያላቸው ግንዛቤ መካከለኛ ነው:: መምህራኑ የአካቶ ትምህርት መርሃ ግብር ከልዩ ፍላጎት በተሻለ መልኩ መምህራንን እንዲዘጋጁ ይረዳል ለሚለው ጥያቄ የሰጡት አማካይ ውጤት 2.79 ሆኖ ስለተገኘ የአካቶ ትምህረት መርሃ ግብር ከልዩ ፍላጎት በተሻለ መልኩ መምህራንን እንዲዘጋጁ ይረዳል በሚለው ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ግንዛቤ አላቸው:: በተመሳሳይ መልኩ የመምህራኑ ምላሽ አማካይ መምህራን በአካቶ ትምህርት ውስጥ የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የበለጠ ሃለፊነት አለባቸው ለሚለው 3.09 ነው:: ስለዚህ የመምህራኑ ግንዛቤ መምህራን በአካቶ ትምህርት ውስጥ የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የበለጠ ሃለፊነት አለባቸው ለሚለው ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል:: በአካቶ ትምህርት ትግበራ ሂደት የሚታዩ ችግሮችን ለመለየት ችግር ፈች ጥናት ማድረግ አዎንታዊ ለውጥ ያመጣል ለሚለው ጥያቄ የመምህራኑ አማካይ ውጤት 2.94 ስለሆነ ስለችግር ፈቺ ጥናት ሚና ያላቸው ግንዛቤ ከፍተኛ ነው:: በተጨማሪም ተማሪዎችን አካቶ ማስተማር ለማህበራዊ ህይወታቸው ትልቅ ፋይዳ አለው ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤት 2.94 መሆኑ ስለዚህ ጉዳይም ያላቸው ግንዛቤ ከፍተኛ ነው :: ቀሪዎችን የግንዛቤ ገለፃ ሠንጠረዥ 4.2 መመልከት ይቻላል ::

የጥናቱ የመጀመሪያ መሪ ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ምን ያህል ግንዛቤ አላቸው? የሚል ሲሆን ይህን ለመፈተሽ በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (one sample t-test)) ተሰልቷል:: ውጤቱም ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ 4.3 ቀርቧል::

ሠንጠረዥ 4.3 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ

| ተላውጦ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | ቲ-ቴስት | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግንዛቤ | 33 | 2.487 | 0.32503 | -0.227 | 32 | 0.822 |

የፍተሻ ዋጋ = 2.5

በሠንጠረዥ 4.3 እንደተመላከተው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ውጤት በ32 የነፃነት ደረጃ (ቲ = -0.227) የፒ-ዋጋ (0.822) ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) የበለጠ በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ ጉልህ ልዩነት አልታየበትም፡፡ አማካይ ውጤቱም (2.487) ሲሆን ከፍተሻ ዋጋ (2.5) ጋር ተመሳሳሰይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ መካከለኛ መሆኑን ነው፡፡

ከጠቅላላ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል 24 (72.7%) መምህራን ስለአካቶ ትምህርት መካከለኛ ግንዛቤ ያላቸው ሲሆኑ የቀሩት 9ኞቹ ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸው እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል (ሠንጠረዥ 4.4) ፡፡

ሠንጠረዥ 4.4: የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ ደረጃ

| የግንዛቤ ደረጀ | ብዛት | በመቶኛ | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|
| መካከለኛ ግንዛቤ ያላቸው | 24 | 72.7 | 2.37 | 0.295 |
| ከፍተኛ ግንዛቤ ያላቸው | 9 | 27.3 | 2.79 | 0.115 |
| ድምር | 33 | 100.0 | | |

### 4.2.1.2 ከፅሁፍ መጠይቅ አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለቀረቡላቸው የተለያዩ የአተገባበር ጥያቄዎች የሰጡት ምላሻች በሠንጠረዥ 4.5 ቀርቧል፡፡ ውጤቱም ከዚህ በታች በዝርዝር ተገልጿል፡፡

ሠንጠረዥ 4.5 የጥናቱ ተሳታፊዎች ስለአካቶ ትምህርት ለቀረቡላቸው የአተገባበር ጥያቄዎች የሰጡት መልሶች

| ጥያቄ | ብዛት | ስሌት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የመደበኛ ስሌት ልኬት |
| የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከሌሎች ጋር አሰባጥሮ በቡድን ማደራጀት ታዘወትራለህ/ሽ | 33 | 2.91 | 0.805 | 0.140 |
| ደከም ያለ የትምህርት አቀባበል ያለባቸውን ተማሪዎችን በአካቶ የትምህርት ሂደት የመርዳት ተሞክሮ አለህ/ሽ | 33 | 2.15 | 0.906 | 0.158 |
| የአካቶ ትምህርትን በቡድን ስራ ይልቅ አቻ ለአቻ መማር አማካይነት በክፍል ዉስጥ ትተገብረለህ/ሽ | 33 | 2.30 | 0.918 | 0.160 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በአካቶ ትምህርት ተማሪዎቹን በቡድናቸዉ ትከታተላለህ/ሽ | 33 | 2.21 | 0.992 | 0.173 |
| ተማሪዎች በቡድን ዉስጥ በበቂ ሁኔታ መንቀሳቀሳቸዉን የመከታተል ልምድ አለህ/ሽ | 33 | 2.30 | 0.984 | 0.171 |
| ለየትምህርት ዓላማ ስኬታማነት በአካቶ ትምህርት እንዲማሩ የተለያዩ አመቺና አሳተፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ትተገብራለህ/ሪያለሽ | 33 | 2.15 | 0.939 | 0.164 |
| የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በቡድን ለክፍሉ እንቀዲያቀርቡ ታደርጋለህ/ሽ | 33 | 2.67 | 0.854 | 0.149 |
| ከትምህርት ቤቱ መምህራን ጋር አካቶ ትምህርትን ለመተግበር ውይይትና ተገቢ ክንውን የማድረግ ተሞክሮ አለህ/ሽ | 33 | 2.91 | 1.071 | 0.186 |
| የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ተነሳሽነትን ለመፍጠር ተጨባጭ ማበረታቻ ትሰጣለህ/ሽ | 33 | 2.82 | 0.769 | 0.134 |
| የተማሪዎችን የመረዳት ሁኔታ በተለያዩ የመገምገሚያ መንገዶች ትጣቀማለህ/ያለሽ | 33 | 2.67 | 0.890 | 0.155 |
| በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ቁጥጥር አካል የአካቶ ትምህርት ትግበራ ላይ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል | 33 | 2.30 | 1.015 | 0.177 |

በሠንጠረዥ 4.5 ከቀረበው መረዳት እንደሚቻለው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከሌሎች ጋር አሰባጥሮ በቡድን ማደራጀት ታዘወትራለህ/ሽ፤ ለሚለው ጥያቄ የመምህራኑ አማካይ ውጤት 2.91 ስለሆነ የመምህራኑ የአካቶ ትምህርት የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከሌሎች ጋር አሰባጥሮ በቡድን ማደራጀት ያላቸው አተገባበር ከፍተኛ መሆኑን ነው። መምህራኑ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በቡድን ለክፍሉ እንቀዲያቀርቡ ታደርጋለህ/ሽ ለሚለው ጥያቄ የሰጡት አማካይ ውጤት (2.67) ሆኖ ስለተገኘ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በቡድን ለክፍሉ እንቀዲያቀርቡ ታደርጋለህ/ሽ በሚለው ጉዳይ ላይ ከፍተኛ አተገባበር አለቸው። በተመሳሰይ መልኩ የመምህራኑ ምላሽ አማካይ ውጤት የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ተነሳሽነትን ለመፍጠር ተጨባጭ ማበረታቻ የመስጠት ትግበራ 2.82 ስለሆነ መምህራኑ የተማሪዎችን ተነሳሽነትን ለመፍጠር ተጨባጭ ማበረታቻ በትምህርቱ ሂደቱ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሰጡ ያመለክታል። እንዲሁም የተማሪዎችን የመራዳት ሁኔታ በተለያዩ የመገምገሚያ መንገዶች በከፍተኛ ሁኔታ እንደተገመገሙ የምላሻቸው አማካይ ውጤት ያሳየ ሲሆን ቀሪዎችን የአተገባበር ገለፃ ሠንጠረዥ 4.3 መመልከት ይቻላል ።

የጥናቱ ሁለተኛ መሪ ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ምን ይመስላል የሚል ነበር። ይህን ለመፈተሽ ይረዳ ዘንድ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (one sample t-test) ተሰልቷል። ውጤቱም ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ 4.6 ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 4.6 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ

| ተላውጦ | የተሳታፊዎች ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | ቲ-ቴስት | የነፃነት ደረጀ | የጉልህነት ደረጀ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግንዛቤ | 33 | 2.4904 | 0.28562 | -0.194 | 32 | 0.847 |

የፍተሻ ዋጋ = 2.5

በሠንጠረዥ 4.6 የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ውጤት እንደሚያሳየው በ32 የነፃነት ደረጃ (ቲ = -0.194) የፒ-ዋጋ (0.847) ከመቁረጫ ነጥቡ (0.05) አንፃር በልጦ በመገኘቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ጉልህ ልዩነት አልታየበትም። አማካይ ውጤቱም (2.490) ሲሆን ከፍተሻ ዋጋ (2.5) ጋር ተመሳሰይ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ውጤት የሚያሳየው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር መካከለኛ ሆኖ መገኘቱን ነው።

በተመሳሰይ መልኩ ከጠቅላላ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል 24 (72.7%) መምህራን ስለአካቶ ትምህርት መካከለኛ አተገባበር ያላቸው ሲሆኑ የቀሩት 9ኞቹ ከፍተኛ አተገባበር እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል (ሠንጠረዥ 4.7)፡፡

ሠንጠረዥ 4.7 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ደረጃ

| የትግበራ ደረጃ | ብዛት | መቶኛ | አማካይ | መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|---|
| መካከለኛ አተገባበር ያላቸው | 24 | 72.7 | 2.36 | 0.208 |
| ከፍተኛ አተገባበር ያላቸው | 9 | 27.3 | 2.83 | 0.132 |
| ድምር | 33 | 100.0 | | |

## 4.2.2 ከቃለ መጠይቅ ግንዛቤና አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና

### 4.2.2.1 ከቃለ መጠይቅ ግንዛቤን የተመለከ የተገኘ ውጤት ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤን መሰረት ባደረጉ በቃለ መጠየቅ የቀረቡ ጥያቄዎች ምላሻቸው ከዚህ በታች ቀርቧል ፡፡ በቃለ መጠይቁም ላይ በቀረቡት ጥያቄ ቁጥር 1 እና 2 ሲሆኑ፣ እንደ ቅደም ተከተላቸው ቀርበዋል ፡፡

አካቶ ትምህርትን እንዴት ትረዳዋለህ (ሺዋለሽ)? ለሚለው ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተሰጡት ምላሾች ሙሉ በሙሉ ባይገሉፁም አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ስለአካቶ ትምህርት ምንነት ሲገልፁ አካቶ ትምህርት ማለት ልዩ ፍላጎት ያላቸውንና የሌላቸውን በአንድ ላይ የማስተማር ዘዴ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡የተቀሩት ጥቂቱ መምህራን አካል ጉዳተኞችን ከአካል ጉዳተኛ አልባ ከሆኑት ጋር ማስተማር መሆኑን ገልፀዋል ፡፡ ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው ተሳታፊዎቹ የሁሉንም ተማሪዎች ልዩነት ታሳቢ አድርገው በአካል ጉዳተኝነት ልዩነት ብቻ ታሳቢ በማድረግ መገንዘባቸውን ነው ፡፡

በተመሳሳይ በጥያቄ 2 በመደበኛ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ዳራ ያላቸውንና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አካቶ ማስተማር በተማሪዎቹ መካከል ምን ጥቅም አለው? ለሚለው ጥያቄ ከ10 ቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ውስጥ 6ቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰጡት ምላሽ አካቶ ትምህርት በተማሪዎች መካከል ማህበራዊ ግንኙነት እንዲፈጠር የሚያበረታታ፣ እኩልነትን የሚያሰፍንና ሁሉም ተማሪዎች ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ዕውቀት እንዲቀስሙ የሚያስችል ሂደት መሆኑን አጽንዖት ሰጥተው መልሰዋል፡፡ ከዚህ ቃለ መጠይቅ ምላሽ መረዳት እንደተቻለው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት መካከለኛ የሆነ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው ፡፡ ከዚህም የቃል መጠይቅ የተገኙ ምላሾችም በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ የተገኘውን ውጤት ያጎላሉ ፡፡

### 4.2.2.2 ከቃለ መጠይቅ አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ የውጤት ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ የተሰጡት የመምህራን ምላሾች ከዚህ በታች ቀርበዋል ፡፡ በዚህ ስር የቀረቡት ጥያቄ ቁጥር 3 እና 4 ሲሆን እንደ በቅደም ተከተላቸው ቀርበዋል ፡፡

የተለያዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዴት አካተው ማስተማር ይችላሉ? ለሚለው ጥያቄ 5ቱ ተሳታፊዎች ሲያብራሩ ተማሪዎቹን አካቶ ለማስተማር የተለያዩ የመርጃ መሳሪያዎችንና የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን በመጠቀም መተግበር እንደሚቻልና በዚሁ አካኂን በጥቂቱ እየተገበሩ እንዳሆነ በሰጡት ሃሳባቸው ውስጥ አንፀባርቀዋል፡፡ ከተሳታፊዎቹ ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው የተለያዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማስተማር የሚጠቀሙበት ጥቂቱን ተግባራትን ብቻ እውን የሚያደርግላቸውን እደሚጠቀሙ ነው ፡፡

እንዲሁም በጥያቄ 4 የቀረበው ፣ አካቶ ትምህርት ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ምን ያስፈለጋል ? የሚለው ሲሆን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ፣ አካቶ ትምህርትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ልዩ ልዩ የመርጃ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ብልሃቶችን ማወቅ እንደሚያስፈልግ በምላሾቻቸው ውስጥ ትኩረት ሰጥተውበታል፡፡ እነርሱም በዚሁ መልኩ እየተገበሩትም እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርትን ትግበራ እንቅስቃሴ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህም የቃለ መጠይቅ ምላሽ የአማርኛ ቋንቋ መምራን የአካቶ ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ የተሰጡት የመምራን ምላሾችም በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ የተገኘውን ውጤት ያጠናክራል ፡፡

### 4.2.3 በክፍል ምልከታ አተገባበርን የተመለከተ የተገኘ ውጤት ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑን አካቶ ትምህርት አተገባበር መሰረት ያደረገ የክፍል ውስጥ ምልከታ ተካሄዷል፡፡ ውጤቱም በሠንጠረዥ 4.8 ቀርቧል

ሠንጠረዥ 4.8: የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበርን የተመለከተ የክፍል ውስጥ ምልከታ

| ተ.ቁ. | ድርጊት | የመምህራን ብዛት | ድግግሞሽ | | በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የለም | አዎን | የለም | አዎን |
| 1 | የእለቱ የቋንቋ ትምህርት አላማ በግለፅ አሳውቋል(ለች) | 10 | 6 | 4 | 60.0 | 40.0 |
| 2 | የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቅሟል(ለች) | 10 | 3 | 7 | 30.0 | 70.0 |
| 3 | አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ አበረታቷል(ለች) | 10 | 7 | 3 | 70.0 | 30.0 |
| 4 | የተማሪዎችን ልዩነት ታሳቢ በማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶችን ተጠቅሟል(ለች) | 10 | 7 | 3 | 70.0 | 30.0 |
| 5 | ሴትና ወንድ ተማሪዎችን እኩል አሳትፏል(ለች) | 10 | 5 | 5 | 50.0 | 50.0 |
| 6 | የተማሪዎችን ስብጥር ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሟል(ለች) | 10 | 4 | 6 | 40.0 | 60.0 |
| 7 | ከፊል የማየት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ምቹነት ያለው የቦታ አቀማመጥ ፈጥራል(ለች) | 10 | 5 | 5 | 50.0 | 50.0 |
| 8 | የተማሪዎችን የመረዳት አቅም በተለያዩ መንገዶች ፈትሾ(ሻ) አግዟል(ለች) | 10 | 1 | 9 | 10.0 | 90.0 |
| 9 | በመምህሩ(ሯ) በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያለው የድምፅ አጠቃቀም ጥሩ ነበር | 10 | 2 | 8 | 20.0 | 80.0 |
| 10 | ተማሪዎች ለሚሰጡት ምላሽ ተመጣጣኝ ማበረታቻ ሰጥቷል (ለች) | 10 | 3 | 7 | 30.0 | 70.0 |

በሠንጠረዥ 4.8 እንደተመለከተው የመምህራን አካቶ ትምህርት ትግባራ ላይ በተከናወነው ምልከታ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የእለቱን የቋንቋ ትምህርት አላማ በግልፅ ከማሳወቅ አንፃር ምልከታ ከተከናወነላቸው 10 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ 6 (60%) መምህራን ያላሳወቁ ሲሆን 4 (40%) መምህራን የእለቱን ትምህርት አላማ በግልፅ

አሳውቀዋል፡፡ የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን ከመጠቀም አኳያ 3 (30%) መምህራን ያልተጠቀሙ ሲሆን 7 (70%) መምህራን ደግሞ ተጠቅሚዋል፡፡ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ ከማበረታትነና ከፊል የማየት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ምቹ ቦታዎችን ከመፍጠር አንፃር 3 (30%) መምህራን ያልተገበሩት ሲሆን 7 (70%) መምህራን ሲተገብሩት ተስተውሏል፡፡ ሌላው በዚህ የክፍል ውስጥ መምልከታ የታየው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን ልዩነት ታሳቢ በማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶችን መፍጠርና ልዩ ልዩ መርጃ መሳሪያዎችን ከመጠቀም አኳያ 7 (70%) መምህራን ያልተገበሩት ሲሆን 3 (30%) መምህራን ሲተገብሩ ታይቷል፡፡ በተመሳሰይ ሴትና ወንድ ተማሪዎችን እኩል ከማሳተፍና የተማሪዎችን የመረዳት አቅም በተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችች ፈትሾ እገዛ ከማድረግ አንጻር 5 (50%) መምህራን ያልተገበሩት ሲሆን 5 (50%) መምህራን ተግብረዋል፡፡ በመምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ጥሩ የድምፅ አጠቃቀምን በተመለከተ 2 (20%) ዝቅተኛ የድምፅ አጠቃቀም ሲታይባቸው 8 (80%) መምህራን መካከለኛ የድምፅ አጠቃቀም ታይቶባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ትግባራን መሰረት አድርጎ በተከናወነው ምልከታ የተገኘው ውጤት (57% )መምህራን የምልከታ መቆጣጠሪያ ቅፅ የተገበሩ ሲሆን (43%) መምህራን አልተገበሩም፡፡ ይህ ውጤት እንደሚያሳየው የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የአካቶ ትምህርት አተገባበር መካከለኛ ነው ለማለት የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡

## 4.2.4. የግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ አድራሾች የተገኘ ውጤት ትንተና

የጥናቱ ሶስተኛው መሪ ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ አድራሾች ምን ምንድናቸው ? የሚል ነው፡፡ ይህንን ለመፈተሽ ይረዳ ዘንድ በቃለ መጠይቅ አባሪ ሐ ጥያቄ 5 ላይ በአካቶ ትምህርት ግንዛቤ እንዳይኖር የሚያደርጉ ተፅዕኖ አድራሾች ምን ምንድናቸው ብለው ያስባሉ? በሚለው ከቃለ መጠይቅ ተሳታፊች የተገኙ ምላሾች ሙሉ ባይሆኑም አብላጫው ተሳታፊዎች አካቶ ትምህርት በተማሪዎች መካከል እኩልነት ለማስፈን የተሸለ የትምህርት አሰጣጥ መሆኑን እንብዛም አለመረዳት ፣ ስራ ላይ ስልጠና አለመሰጠት ፣ አቻ ለአቻ መምራን የልምድ ልውውጥ አለማድረግ ፣ በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እገዛ የአካቶ ትምህርት በበቂ ሁኔታ መስጠትን አለመረዳት ፣ የአካቶ ትምህርት ፅንሰ ሀሳብ በስፋት አለመገዘብ ፣ በአካቶ ትምህርት ላይ ችግር ፈቺ ጥናቶች ያለማድረግ ፣የሚሉትን ዘርዝረዋል ፡፡ ከዚህ ምላሽ

መረዳት እንደሚቻለው ከዚህ በላይ የዘረዘሩት በአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቶ ትምህርት ግንዛቤያቸው ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው ነው ፡፡

በተጨማሪም በአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ አድራሾችን በሚመለከት የፅሁፍ መጠይቅ ተሳታፊዎች የሰጡት ምላሽ አማካይ ውጤቱና መደበኛው ልይይት ውጤት በቃለ መጠየቅ የተገኘውን ውጤት የሚያጎላ ነው ፡፡

በተመሳሳይ በአካቶ ትምህርት አተገባበር ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ብለው የሚያስቡ ነገሮች ምን ምንድናቸው ?ለሚለው ጥያቄ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተሰጡት ምላሾች አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች የትምህርቱን አላማ በበቂ ሁኔታ አለመተግበር ፣ በተለያዩ ቴክኖሎጂ ውጤቶች እገዛ አካቶ ትምህርትን እንብዛም አለመስጠት ፣ አመቺና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በበቂ ሁኔታ አለመጠቀም ፣ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በሰፊው አለመጠቀም ፣ የተማሪዎችን ስብጥር ከግምት ውስጥ አስገብቶ በቅጡ አለመተግበር ፣ የመማር ማስተማር ቁጥጥር አካል ክትትልና ድጋፍ በበቂ ሁኔታ አለማድረግ ፣ በተናጥልና በቡድን ተማሪዎችን በብዛት አለማሳተፍ ከወላጅ ጋር ተቀራርቦ የመወያየትና ችግርን ለይቶ መፍትሄ ያለመስጠት እንደሆኑ ገልፀዋል ፡፡ ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው  የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአካቶ ትምህርት አተገባበር ላይ አሉታዊ ተፅዕው እንዳሳደረባቸው ነው ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በፅሁፍ መጠይቅና  በክፍል ምልከታ የተገኙት ውጤቶች ከላይ የተዘረዘሩት አማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቶ ትምህርት አተገባበር ላይ ተፅዕኖ አድራሾች መሆናቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያጎላሉ ፡፡

## 4.3 የውጤቱ ማብራሪያ

የዚህ ጥናት የመጀመሪያ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ ደረጃንና መጠን መመርመር የሚል ሲሆን ይህንንም ለመለየት ይረዳ ዘንድ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ (one sample t-test) ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ውጤቱም በ32 የነፃነት ደረጃ (ቲ=-0.227) የፒ-ዋጋ (0.822) ከመቁረጫ (0.05) ነጥብ በልጦ በመገኘቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ ጉልህ ልዩነት አልታየበትም፡፡ አማካይ ውጤቱም (2.487) ሲሆን ከፍተሻ ዋጋ (2.5) ጋር ሲታይ ተመሳሰይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንን ውጤት በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች መጠናዊ እና ዓይነታዊ ትንተናም ውጤቱን አጉልቷል፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት ከአገር ውስጥ ጥናቶች ከካሴ (2013) እና ከታደሰ (2014) የጥናት ውጤት ጋር ሲደጋገፍ ከውጭ አገር ደግሞ ከአልሃሰን (2014) ጥናት ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡ እነዚህ ምሁራን በጥናታቸው እንዳመላከቱት መምህራን

ስለአካቶ ትምህርት ምንነትና ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ መካከለኛ የሚባል እንጂ ከፍተኛ ለማለት የሚያስደፍር እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

ሁለተኛ የጥናቱ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል መመርመር ነበር፡፡ ውጤቱ የተፈተሸው በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ (one sample t-test )ና በመቶኛ ስሌትና በገለጻ ነው፡፡ የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ውጤት እንደሚያሳየው በ32 የነፃነት ደረጃ ( ቲ = -0.194 ) የፒ-ዋጋ ( 0.847 ) ከመቁረጫ ነጥቡ ( 0.05 ) አንፃር በልጦ በመገኘቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ጉልህ ልዩነት አልታየበትም ፡፡ አማካይ ውጤቱም ( 2.490 ) ሲሆን ከፍተሻ ዋጋ ( 2.5 ) ጋር ሲነፃፀር ተመሳሰይ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር መካከለኛ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ውጤት በቃለ መጠይቅና በክፍል ውስጥ ምልከታ ቼክሊስቶች በተሰበሰበው መረጃዎች ውጤት ተጠናክሯል፡፡ ምክንያቱም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ምልከታ በመቶኛ ስሌት ውጤት (57%) ያህል መምህራን የአካቶ ትምህርትን እንደተገበሩ ሲያሳይ ቀሪዎቹ (43%) አካቶ ትምህርትን አልተገበሩም፡፡ በመሆኑም ይህ ውጤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር መካከለኛ እንደሆነ አጉልቶታል፡፡

ሶስተኛው የጥናቱ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩት ምን ምንድናቸው ? የሚለውን ለመፈተሽ የዋለ ሲሆን ይህንን ለመለየት ይረዳ ዘንድ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአይነታዊ መንገድ ተተንትነዋል ፡፡ ውጤቱም በአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ አካቶ ትምህርት በተማሪዎች መካከል እኩልነት ለማስፈን የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አለመረዳት፣ የስራ ላይ ስልጠና አለመሰጠት፣ በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እገዛ የአካቶ ትምህርት በበቂ ሁኔታ መሰጠትን አለመረዳት፣ አመቺና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በበቂ ሁኔታ አለመጠቀም ፣የተለያዩ መርጃ መሳሪያ እንበዛም አለመጠቀም፣ የተማሪዎችን ስብጥር በበቂ ሁኔታ ግምት ውስጥ አለማስገባት፣ የቁጥጥር አካል ክትትልና ድጋፍ እንብዛም አለማድረግ የሚሉተን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ይህ ውጤት የሚያመላክተው በአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ መሆናቸውን ነው ፡፡

ውጤቱም ከካሴ (2013) እና ከአልሃሰን (2014) የጥናት ውጤቶች ጋር ሲነፃፀር የተለያየ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም ምሁራኑ በጥናት ውጤታቸው እንደገለጹት በእነርሱ ጥናት የተሳታፉት መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር ዝቅተኛ ስለሆነ ነው፡፡

ይህ ጥናት ከእነዚህ ጥናቶች የሚለየው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎችን ልዩነት ታሳቢ አድርገው አካቶ ትምህርትን ከመገንዘብና ከመተግበር አንፃር ውጤቱ ምን ምን እንደሚመስልና ተፅዕኖችን በመፈተሽ ላይ ያተከረ ነው ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5፡ ማጠቃለያ፣ መደምደምያና አስተያየት

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ በጥናቱ የተደረሰበት መደምደሚያና የመፍትሔ ሃሳቦች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር መፈተሽ ነበር፡፡ በመሆኑም ጥናቱ እንዲመልሳቸው የተፈለጉ መሰረታዊ ጥያቄዎ የሚከተሉት ነበሩ፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራ በአካቶ ትምህርት ላይ ያላቸው ግንዛቤ ምንያህል ነው?
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራ የአካቶ ትምህርት አተገባበር ምን ይመስላል?
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ተፅዕኖዎች አድራሾች እነማናቸው?

እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ መመለስ እንዲቻል በመጀመሪያ የጥናቱ ተሳታፊዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል፡፡ ተሳታፊዎቹ በ2013 ዓ.ም በምስራቅ አርሲ ዞን ካሉት ወረዳዎች አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ በቀላል እጣ ማውጣት ናሙና የተመረጡ 25 ሴትና 8 ወንድ በድምሩ 33 መምህራን ናቸው፡፡ ጥናቱን በተሳካ መንገድ ለማከናወን መረጃዎቹ በፅሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታና በቃለመጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡

በፅሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች “SPSS Version 21” ሶፍትዌርን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ ይህም የፅሁፍ መጠይቅ መረጃዎች በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (one sampel t-test) እና ገለፃን በመጠቀም የተተነተኑ ሲሆን በምልከታ የተገኙ መረጃዎች በመቶኛ ስሌትና በገለፃ ተተንትነዋል፡፡ እንዲሁም በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በገለፃ ብቻ ተንትነው ቀርበዋል፡፡

በመሆኑም የአማርኛ ቋንቋ መምህርን በአካቶ ትምህርት ግንዛቤ ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽ በፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ (one sampel t-test) ውጤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ አማካይ ውጤት (2.48) በመሆኑ ከፍተሻ ዋጋ አማካይ ውጤት (2.5) ጋር ሲታይ

ተመሳሳይ ሆኖ ስለተገኘ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ መካከለኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበር አማካይ ውጤት (2.49) ሲሆን ከፍተሻ ዋጋ (2.5) ጋር ሲነፃፀር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት እንዳመለከተው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት አተገባበራቸው መካከለኛ እንደሆነ ከጥናቱ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ በአካቶ ትምህርት በተማሪዎች መካከል እኩልነት ለማስፈን የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አለመረዳት፣ የስራ ላይ ስልጠና አለመሰጠት፣ በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እገዛ የአካቶ ትምህርት በበቂ ሁኔታ መሰጠትን አለመረዳት፣ አመቺና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በበቂ ሁኔታ አለመጠቀም ፣የተለያዩ መርጃ መሳሪያ እብዛም አለመጠቀም፣ የተማሪዎችን ስብጥር በበቂ ሁኔታ ግምት ውስጥ አለማስገባት፣ የቁጥጥር አካል ክትትልና ድጋፍ እብዛም አለማድረግ የሚሉተን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

## 5.2. መደምደምያ

በአጠቃላይ በጥናቱ ትንተና ውጤት መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤና አተገባበር መካከለኛ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡ ስለሆነም የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለአካቶ ትምህርት ያላቸው ግንዛቤ የመካከለኛነት ደረጃ ይዟል፡፡ ይህም መምህራኑ ስለ አካቶ ትምህርት የተወሰነ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ለአካቶ ትምህርት ስኬታማነት የመምህራን ግንዛቤ ትልቁን ድርሻ የሚይዝ በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከሚጠበቅባቸው የአካቶ ትምህርት ግንዛቤ ደረጃ እንዳልደረሱ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት ያላቸው አተገባበር መካከለኛ እንደሆነ በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡ ይህም የሚያመላክተው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቶ ትምህርት ከመተግበር አንፃር ጅማሮ ያላቸው ቢሆንም በቂ ነው ለማለት የማያስደፍር መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡
3. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድርባቸው አካቶ ትምህርት በተማሪዎች መካከል እኩልነት ለማስፈን የተሻለ

የትምህርት አሰጣጥ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አለመረዳት፣ የስራ ላይ ስልጠና አለመሰጠት፣ በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እገዛ የአካቶ ትምህርት በበቂ ሁኔታ መሰጠትን አለመረዳት፣ አመቺና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በበቂ ሁኔታ አለመጠቀም ፣የተለያዩ መርጃ መሳሪያ እንበዛም አለመጠቀም፣ የተማሪዎችን ስብጥር በበቂ ሁኔታ ግምት ውስጥ አለማስገባት፣ የቁጥጥር አካል ክትትልና ድጋፍ እንብዛም አለማድረግ የሚሉተን በጥናቱ ታይቷል። ይህም የሚያመለክተው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አካቶ ትምህርት የተወሰነ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ከአተገባበር አንፃር ጅማሮ ላይ እንዲሆኑ ተፅዕኖ እንዳደረሰባቸው ጥናቱ አሳይቷል።

## 5.3. አስተያየት

ከጥናቱ ውጤት፣ ማብራሪያና መደምደሚ በመነሳት የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል።

1. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቶ ትምህርትን በተመለከተ የተለያዩ የስራ ላይ ስልጠናዎችን በመስጠት የግንዛቤ ደረጃቸውን ማሻሻል ይቻላል። መምህራን የተማሪዎችን ልዩነት እንዲረዱና ልዩነታቸውን ታሳቢ አድርገው በክፍል ውስጥ አካተው እንዲያስተምሩ የስራ ላይ ስልጠና ቢሰለጥኑ የተሻለ ይሆናል። በመሆኑም መምህራን አሁን ካሉበት የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና የአተገባበር ደረጃ ከፍ እንዲሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ስልጠና ቢሰጧቸው፤
2. መደበኛ መምህራን ከልዩ ፍላጎት መምህራን ጋር ህብረታዊ ስራን በመፍጠር የአካቶ ትምህርት ግንዛቤያቸውንና የአተገባበር ደረጃቸውን ሊያሳድጉ ይችላሉ። ስለዚህ በመምህራን መካከል የአቻ ለአቻ የልምድ ልውውጥ እንዲከናወን የትምህርት ቤት አስተዳደር አካላት ዕድሎችን ቢያመቻቹ፤
3. ለአካቶ ትምህርት ትግበራ ስኬታማነት ከመምህራን ግንዛቤ በተጨማሪ የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች መሟላት ትልቁን ሚና ይጫወታሉ። ስለዚህም መምህራን የተማሪዎችን ልዩነት አካተው ለማስተማር ያግዛቸው ዘንድ የትምህርት ቤት አስተዳደሮችና የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ አካላት የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን (ብሬል፣ ቴፕሪከርደር፣ ቻርት ወዘተ) ቢያሟሉላቸው ፤
4. የአካቶ ትምህርትን ግንዛቤ ለማስፋት የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ለርዕሰ ጉዳይ ሰፊ ሽፋን ቢሰጡ ፤
5. በመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጣቸው ግን ፆታ ፣ የማስተማር ልምድ፣

የማስተማሪያ ዘዴ ማስተማሪያ መሳሪያዎችና የስራ ላይ ስልጠና ናቸው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ጥናት ማካሄድ የሚሹ ተመራማሪዎች በእነዚህና በዚህ ጥናት ባልተዳሰሱ ሌሎቸ የመምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበር ላይ ተፅዕኖ በሚያሳድሩ ነገሮች (በትምህርት ደረጃ፣ በዕድሜ …ወ.ዘ.ተ) እና በሌሎች ለአካቶ ትምህርት ስኬታማነት ወሳኝ በሆኑ ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ቢያካሂዱ ለአካቶ ትምህርት ትግበራ ውጤታማነት ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

## ዋቢዎች


ትምህርት ሚኒስተር፡፡ (2004) ፡፡ የልዩ ፍላጎት (አካቶ) ትምህርት ስትራቴጂ፡፡ አዲስ አበባ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡

ያለው እንዳወቁ፡፡ (2004) ፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ 3ኛ እትም፣ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ ንግድማተሚየ ድርጅት፡፡

አለማየሁ ተ/ማርያም፡፡(2016)፡፡ በመተባበር መማር፡፡ ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር፡፡

Alhassan, A. M. (2014) Implementaion ofinclusive eduction in Ghanaian primary schools Alook at teachers attitude; American Joumal of Educational Research, 2(3), 142-148.

Al-Katteeb, J. (2002). Teachers percveptions of the inclusive school concept in Jordan. Educational Joumal, 65, 19-39.

Armstrong, F. (2004). The inclusive school. A paper presented to proceeding Of the joint conference of the irish teachers organization and equality, Limerick 27 th March,2004. Retrived from

Armsstrong, F.(2004). The inclusive school. A paper preented to proceeding of the Joint Conference of the irish teachers Organization and equality, Limerick 27th March, 2004. Retrived from. http;//www.info.ie/Rol/inclusive school.Pdf.

Aserat, D.(2013). Factors Affecting the Implementation of Inclusive EEducation inprimary schools of Bahir Dar Town Adminstration. Education Research Journal,3(3):pp.59-67.

Avramids, E., & Norwich, B.(2002). Teachrs attitudes to wards

Integration/ nclusion: Areviwe of Literature. European Journal of special Needs Education, 17(2),129-147.

Baker. J.M., & Zigmond, N. (19950. The Meaning of and Practice of Inclusion for students with learning disabilities. Jouranal of special Education, 29(2), 163-180

Ben-pajooh. A. (1992). The Effect of social contact on college teachers attitudes towards student with severe mental handicaps and their educational integration. European Journal of special needs Education, 7,231-236

Brakenreed, D.(2011). Inclusive education: identifiying teachers Stratigies for coping with perceived stressorsin inclusive classroom. Canadian journal of Education Administration and Policy, 122,1-137.

DeBore. A.Pijil, J., & Minnaert, A.(2011). Regular primary school Teachers Attitudes towards Inclusive Education: A Reviwe of the Literature. Interanational Journal of inclusive Education. 15(3), pp,331-353

Department of Education and Skills,.(2010). Development of a Framework for action for the Inclusion of children with special Needs in Early childhood EEducation setting. (pp.1-24).

Dyson, A. and Millward, A. (2000). Schools and Special Needs. Issues of Innovation Inclusion. Paul chapman publishing Ltd.

Eortin C Cediflo. I, G.Romero-contreas, s. Fletcher. & Hemandez. H(2010). Inclusionin Mexico Ensuring Supporting attitudes by newly graduated teachers, interanational icurnal of inclusive Education. 14, 723-739.

Etenshe A. (2000). Situtional analaysis of Ethiopia. Unpublished report.

Foriin, C., Tait, K., Carroll, A. & Jobling, A. (1999b). Teacher education for diversity. Queensland Joumal of Educational Research, 15(2), 207-225

Fuchs, W. (2010). Examining teachers Percived barriers associated with inclusion. SRATE Joumal, 19(1), 30-35.

Gal, E., Schreur N., & Engel-Yeger, B.(2010). Inclusion of children with Disbilities, teachers attitudes and requirements for environment accommodation. International Joumal of special Education, 25(2).

Greene, L.,(2017). Teachrs Attitudes Towards Inclusive class room. Walden University.

Gokder M.(2012), A comparative Study of the Attitude. Concern and interaction Levels of Elementary Schools Teacher candidates to wards inclusive Education. Educational science; Theory and practice. 12, 1303-0485

Hattie, J. 92009). Visible learning. London, Uk; routledge.

Hay, J.F., Smit, J., & Paulsen, M. (2002). Teachre preparedness for InclusiveEducation. South African Journal of Eeducational, 21, 213-218.

Hui Ng, M.S. (2015). Factors influencing the Success of inclusive practices in singaporean schools. Universitise; Oslo.

Jennifer, K.H.(2015). Teachre Attitudes; An Analysis of Middel school Teachrs Attitudes Towards Inclusion.

Jordan, A., Carlile, & Stack., A.(2008). Approaches to learning.

Kassie, S.(2013). Inclusive Teaching involving Visually Impired Students inEnglish Language Teaching(ELT) Settings. Unpublished Doctoral Dissertation, university of Andharan.

Katrian, A.R.(2006). Vygotsky methodology for inclusive education. Norway university of Oslo.

Kern, E.(2006). Asurvey of Teacher Attitude Regarding inclusive Education within An urban School District. From

http.//digitalcommons, edu/Psychology-dissertation:

Marchiesi, A.(1998). International perspectives on Special education reform European. Journal of special needs Education. 13, 116-122

Mastropieri, M. A, & Scruggs, T. E. (2001). Promoting inclusion in secondary Class Room. Learning Disability quarterly, 24(4), 265-27

Ministry of education. (2016) Special Needs Education program strategy. Emphasising inclusive education to meet the UPEC and EFA goals, Ministry of Education, Addis Ababa

Oliver, P. (1996). Education for all? Prespective on an inclusive society. In M. Oiver(Ed.), Understnding Disability. From Theory to practive (pp.78-94). Basingstoke Macmillan.

Pljil S J., Moijer, C, J. W and Hegarty, S.(Ede)(1997)inclusive Education. A Global Agenda. Londer Houtledge taylor & Francis Group.

Regmi, N.P(2017). Inclusive Education in Napal from Theory to Practice Bajura.

Rise (2008) Implementing Inclunive Education. Aommon wealth culde to implementing Article 24 of the UN Convention on the flighte of people With Disabilties. Cahrles Worth Group.

Rubinshtein, s. (1979). Psikhologia Umstvenno otstalogo shkotnika (Psychology of Mentally Retarded student). Moscow prosveschchenle press.

Salend. S., & Duhaney, L.G. (1999). The Impact of inclusion on students with and with out disabilities. Remedial and Special Education. 16(5), 271-278.

Sharma, U., Forlin, C. & Loroman, (2008). Impact of Training on preservice Teacher's attitudes and concerns about inclusive education and Sentiments about persons with disabilities, Desability and Society, 23, 773-785.

Slavica, P.(2010). Inclusive education Proclamationor reality primary schools teachers viow. Us-china Education Reviwe. 7(10). 62-69>

Tadese Z. (2014).The knowled Attitudes and Practice of inclusive education in North Wollo Zone rular primary schools. Doctoral disselration, university of indira Gondhi.

Tefera, T.(1999). Inclusion of children with Disabilites in Regular schools: challenges and Opportunities. The Ethiopian Journal of Education XIX(1) Institute of Educational Researcher. AAu Printing press.

Thomas, G., Walker, D. & Webb,j.(2005). Inclusive education: the ideals and the Practice in Topping, K. and Maloney, s.(Eds.), The Routledge Falmr Readin inclusive Education. (pp17-28). London, Routledge Falmer.

Tibehu B. (1995). Meanlings attached to disability attitudes towards disable, atituds towords interpration.

Tirusswe, T. (2006). Overview of the development of inclusive education in the last Fifteen years in Ethiopia in Savolainen, H, Matero, M and Kokkala, H. (eds), When All Means All: Exeriesnces in Three African Countries With EFA And Children With Disabilities, Ministre for Foreign Affairs of Finland, Helsiniki.

Unesco. (1994). The Salamancaa statement and Frame Work For Action on special Needs Ethiopia. Pariis. Unesco

------------(2003). Overcoming Excusion through Inclusive Approaches in Education. A Challenge and avision: Conceptual paper. France: UNESCO.

---------(2005). Gude Lines for Inclusion Ensuring Access to Education for All. France: UNESCO.

Unianu, M.E.(2011). Teachers' attitudes to wards inclusive education Social and Behavioral sciences, 33(2012), 900-904.

Vygotsky, L.(1993). The collected Work of L.S. Vygotsky. Vol.2: The Fundamental of defectology (abnormal Psychology and learning disabilities) (R.W.Rieber & A.S.Car-ton, Eds.).NY:plenum press.

World Vision.(2007). Including the Excluded: Integrating disability into the EFA Fast Track intiative Processes and National Education Plans in Ethiopia. World Vision UK: Milton Keynes.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ፡ የፅሑፍ መጠይቅ

## ጅማ ዩኒቨርሲት

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ፋካልቲ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መረሀ ግብር

ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የተዘጋጀ የፅሑፍ መጠይቅ ወድ መምህራን፡- አንድ ጥናት የታሰበውን ችግር ለመፍታት የሚችለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው የተዋጣለት በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ጥናቱ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ለጥያቄዎቹ እውነተኛ መረጃ መስጠት የቻሉ እንደሆነ ጭምር ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ የዚህ የፅሑፍ መጠይቅ ዓይተኛ ዓለማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባባር ምን እንደሚመስል ለመመርመር የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም እርሶም በዚህ መጠይቅ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ሁሉ ደህንነታቸው የተጠበቀ ለጥናቱ አግለግሎት ብቻ የሚውሉ መሆነቸውን አውቀው እያንደንዱን ጥያቄ በጥሞና በማንበብ ሀሳቦትን አስፍሩ

ማሳሰቢያ፡-

- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አስፈላጊ አይደለም፡፡
- መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባው የተከለከለ ነው፡፡

ክልል አንድ → የመምህራን አስፈላጊ ገላጭ ማስረጃዎች

መመሪያ 1 ከተራ ቁጥር 1-5 ለተዘረዘሩት ነጥቦች በሚስማማህ/ሽ ላይ በሳጥን ምልክቶች ውስት የ “X”ምልክት አድሪግ/ጊ፡፡

1. ፆታ → ሴት ☐ ወንድ ☐
2. እድሜ 20-30 ☐
   31-40 ☐
   41-50 ☐
   51-60 ☐

የትምህርት ደረጃህ/ሽ

- የመጀመሪያ ድግሪ ያላጠናቀቀ/ች ☐
- የመጀመሪያ ድግሪ ያጠናቀቀ/ች ☐
- ሁለተኛ ድግሪ ያላጠናቀቀ/ች ☐
- ሁለተኛ ድግሪ ያጠናቀቀ/ች ☐
- ከሁለተኛ ድግሪ በላይ ☐

3. አሁን እያስተማርክ/ሽ ያለህበት/ያለሽበት የክፍል ደረጃ

   9ኛ-10ኛ ☐

   11ኛ-12ኛ ☐

4. በመምህርነት ሙያ ላይ ያለህ/ሽ ቆይታ

   1-10 ☐ 11-20 ☐

   21-30 ☐ ከ30-ዓመት በላይ ☐

ክፍል ሁለት

መመሪያ 2 ከዚህ በታች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤና አተገባበርን የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ከጥያቄ 1-13 ድረስ ያሉት የመምህራኑን የአካቶ ትምህርት ግንዛቤን ገፅታ ሲዳስሱ፤ ከጥያቄ 14-24 ያሉት ደግሞ የመምህራንን አካቶ ትምህርት አተገባበር የሚመለከቱትን ይዳስሳሉ፡፡ እንዲሁም ጥያቄዎች የተዘራዘሩበት ነጥቦች ደግሞ፤የመምህራኑን የአካቶ ትምህርት አማራጮች፤ ማለትም በጣም እስማማለሁ(4)፤ እስማማለሁ(3)፤ አልስማማም(2) እና በጣም አልስማማም(1) በሚል ለሁለቱም የጥየቄ ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም የእርሶዎን አተገባበርና ግንዛቤያን ያንፀባርቃል በሚሉት ሀሳብ ትይዩ ባሉት አማራጮች ላይ የ“X” ምልክት ያድርጉ፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክል ወይም ስህተት መልስ የለውም፡፡

| ተ.ቁ | የመምህራንን የአካቶት ትምህርት ግንዛቤ የሚመለከቱ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | (4) | (3) | (2) | (1) |
| 1 | አካቶ ትምህርት የተማሪዎችን እኩልነት ለማስፈን የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ ነው፡፡ | | | | |
| 2 | አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከአካል ጉዳተኛነት አልባ ተማሪዎች ጋር አካቶ ማስተማር ይቻላል | | | | |
| 3 | የአካቶ ትምህረት መርሃ ግብር ከልዩ ፍላጎት በተሻለ መልኩ መምህራንን እንዲዘጋጁ ይረዳል፡፡ | | | | |
| 4 | መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት እና ችሎታ ታሳቢ ማድረግ አለባቸው | | | | |
| 5 | መምህረን በአካቶ ትምህርት ውስጥ የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የበለጠ ሃለፊነት አለባቸው፡፡ | | | | |
| 6 | አካቶ ትምህርት በተማሪዎች መካከል የመገለል ሁኔታ እንዳይፈጠር ያረጋል | | | | |
| 7 | በተለያዩ የቴክኖሎጂ ዉጤቶች (ኮንፒዉተር ፤ የድምፅ መሳሪያዎች----ወዘተ) እገዛ የአካቶ ትምህርት በትምህርት ቤትህ/ሽ ይሰጣል | | | | |
| 8 | መምህራን አካቶ ትምህርትን ለመተግበር ልዩ የስራ ላይ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡ | | | | |
| 9 | በአካቶ ትምህርት ትግባራ ሂደት የሚታዩ ችግሮችን ለመለየት ችግር ፈች ጥናት ማድረግ አዎንታዊ ለዉጥ ያመጣል | | | | |
| 10 | የትምህርት ቤትህ/ሽ አስተዳዳር ለአካቶ ትምህርት ክንዉን ተጨባጭ ድጋፍ (በቁሳቁስ ፣ በገንዘብ ፣ በክህሎት) ያደርጋል፡፡ | | | | |
| 11 | ከማህበረሰብ ጋር ቁርኝት ፈጥረህ/ሽ በአካቶ ትምህርት ዙሪያ ተገቢ መሻሻሎችን የሚስተዋሉበት አውድ አድብረሀል/ሻል | | | | |
| 12 | ተማሪዎችን አካቶ ማስተማር ለማህበራዊ ህይወታቸው ትልቅ ፈይዳ አለው፡፡ | | | | |
| 13 | በአካባቢህ/ሽ ያሉ መንግስታዊና መግስታዊ ያልሆኑ ግብረሰናይ ድርጅቶች ለአካቶ ትምህርት ተግባር ድርሻቸው ብዙም አይደለም | | | | |

| ተ.ቁ | የመምህራንን የአካቶት ትምህርት አተገባበር የሚመለከቱ | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 14 | የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ከሌሎች ጋር አሰባጥሮ በቡድን ማደራጀት ታዘወትራለህ/ሽ | | | | |
| 15 | ደከም ያለ የትምህርት አቀባበል ያለባቸዉን ተማሪዎችን በአካቶ የትምህርት ሂደት የመርዳት ተሞክሮ አለህ/ሽ | | | | |
| 16 | የአካቶ ትምህርትን በቡድን ስራ ይልቅ አቻ ለአቻ መማር አማካይነት በክፍል ውስጥ ትተገብረለህ/ሽ | | | | |
| 17 | በአካቶ ትምህርት ተማሪዎቹን በቡድናቸው ትከታተላለህ/ሽ | | | | |
| 18 | ተማሪዎች በቡድን ውስጥ በበቂ ሁኔታ መንቀሳቀሳቸውን የመከታተል ልምድ አለህ/ሽ | | | | |
| 19 | ለየትምህርት ዓላማ ስኬታማነት በአካቶ ትምህርት እንዲማሩ የተለያዩ አመቺና አሳተፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ትተገብራለህ/ሪያለሽ | | | | |
| 20 | የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በቡድን ለክፍሉ እንቀዲያቀርቡ ታደርጋለህ/ሽ | | | | |
| 21 | ከትምህርት ቤቱ መምህራን ጋር አካቶ ትምህርትን ለመተግበር ዉይይትና ተገቢ ክንውን የማድረግ ተሞክሮ አለህ/ሽ | | | | |
| 22 | የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ተነሳሽነትን ለመፍጠር ተጨባጭ ማበረታቻ ትሰጣለህ/ሽ | | | | |
| 23 | የተማሪዎችን የመረዳት ሁኔታ በተለያዩ የመገምገሚያ መንገዶች ትጣቀማለህ/ያለሽ | | | | |
| 24 | በትምህርት ቤቱ የመማር ማስተማር ቁጥጥር አካል የአካቶ ትምህርት ትግበራ ላይ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል | | | | |

# አባሪ ለ፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ ቼክሊስት

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ፋካልቲ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መረሀ ግብር

ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የተዘጋጀ  የክፍል ምልከታ ቼክሊስት

የመምህራንን የአካቶ ትምህርት አተገባበር መሰረት ያደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታ

የትምህርት ቤቱ ስም ----------------------------------------

የመምህሩ/ራ ስም ----------------------------------------

የትምህርት ደረጃ ----------------------------------------

የምልከታው የክፍል ደረጃ ----------------------------------------

የምልከታው ቀን-----------------------የምልከታው ቆይታ --------------------------------------

የተማሪዎች ብዛት ----------------------------------------ወንድ-----------------ሴት

መመዘኛዎች            አዎ -1                    የለም - 0

| ተ.ቁ | አካቶ ትምህርት ትግበራን የተመለከቱ መመዘኛ ቼክሊስት | 0 | 1 |
|---|---|---|---|
| 1 | ስለዕለቱ ትምህርት ዓላማ በግልጽ አሳወቋል(ለች)፡፡ | | |
| 2 | የተለያዩ የማስተማሪያ ብልሃቶችን ተጠቀሟል(ለች)፡፡ | | |
| 3 | የተለያዩ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንዲሳተፉ  አበረታቷል(ታለች)፡፡ | | |
| 4 | የተማሪዎችን ልዩነት ታሳቢ በማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶችን ተጠቅሟል(ለች)<br>• በጥንድ<br>• በትንንሽ ቡድን | | |
| 5 | ሴትና ወንድ ተማሪዎን እኩል አሳትፏል(ለች)፡፡ | | |
| 6 | የተማሪዎችን ስብጥር ግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን ተጠቅሟል(ለች)፡፡ | | |
| 7 | ከፊል የማየት ችግር ላለባቸው ተማሪዎ ምቹነት ያለው የቦታ አቀማመጥ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ፈጥሯ(ለች)፡፡ | | |
| 8 | የተማሪችን የመረዳት አቅም በተለያዩ የመገምገሚያ መንገዶች ፈትሾ(ሻ) አግዟል(ዛለች)፡፡ | | |
| 9 | መምህሩ(ሯ) በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተመጣጣኝ የድምፅ አጠቃቀም ነበረው(ራት)፡፡ | | |
| 10 | ተማሪዎች ለሚሠጡት ምላሽ ተመጣጣኝ የሆነ ማበረታቻ ተሰጥቷል፡፡ | | |

# አባሪ ሐ ፡ቃለ መጠይቅ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ፋካልቲ የአማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መረሀ ግብር

የመምራን አካቶ ትምህርት ግንዛቤ እና አተገባበር ለመፈተሽ የሚወሉ ቃለ መጠይቆች

ክፍል አንድ ገላጭ ማስረጃዎች

1. የተጠቂው ስም ______________________

   ቃለ መጠይቁ የሚከናወንበት ቀን ______________________
2. ቃለመጠይቁ የሚከናወንበት ቦታ ______________________
3. የቆይታ ጊዜ ______________________

   ክፍል ሁለት፡- መምህራን አካቶ ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤና አተገባበር በተመለከተ ምላሽ የሚሰጡባቸው ጥየቄዎች

1. አካቶ ትምህርት እንዴት ትረዳዋለህ /ዋለሽ ?-------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ----------------------------------------------------------::
2. በመደበኛ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ዳራ ያላቸውንና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አካቶ ማስተማር ምን ጥቅም አለው ?------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------::

3. የተለያዩ ፍላጎት ያለቸውን ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ምህራንን እንዴት አካተው ማስተማር ይችላሉ ?-----------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
-------------::

4. አካቶ ትምህርትን ውጤታማ በሆነ መልኩ መተግበር ምን ያስፈልጋል ?----------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------::

5 በአካቶ ትምህርት ግንዛቤ እንዳይኖር የሚያደርጉ ተፅዕኖ አድራሾች ምን ምንድናቸው ብለው ያስባሉ ?---------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------::

6 በአካቶ ትምህርት አተገባበር ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ብለው የሚያስቡት ነገሮች ምን ምንድናቸው ?--------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------::

# አባሪ መ፤ የፅሑፍ መጠይቅ ውጤት

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶትምህርት ግንዛቤን የተመለከተ የየፅሑፍ መጠይቅ ውጤት

| መለያ | ግ | ግ2 | ግ3 | ግ4 | ግ5 | ግ6 | ግ7 | ግ8 | ግ9 | ግ10 | ግ11 | ግ12 | ግ13 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| AMA001 | 2 | 2 | 3 | 1 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 4 | 2 |
| AMA002 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 |
| AMA003 | 2 | 2 | 1 | 1 | 4 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 |
| AMA004 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| AMA005 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 |
| AMA006 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 1 | 4 | 2 |
| AMA007 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 1 | 1 | 4 | 2 |
| AMA008 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 |
| AMA009 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 |
| AMA010 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 |
| AMA011 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 1 |
| AMA012 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 1 | 4 | 1 |
| AMA013 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 3 | 2 |
| AMA014 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| AMA015 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 1 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 |
| AMA016 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 |
| AMA017 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 4 | 3 | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 |
| AMA018 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 |
| AMA019 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| AMA020 | 2 | 1 | 4 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 |
| AMA021 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| AMA022 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 |
| AMA023 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 |
| AMA024 | 1 | 1 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| AMA025 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| AMA026 | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 |
| AMA027 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 |
| AMA028 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 2 | 1 |
| AMA029 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 |
| AMA030 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 | 1 | 2 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| AMA031 | 2 | 3 | 4 | 1 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 |
| AMA032 | 3 | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 | 3 | 1 | 4 | 2 | 1 | 3 | 4 |
| AMA033 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 |

## የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የአካቶትምህርት አተገባበር የፅሑፍ መጠይቅ ውጤት

| መለያ | አ01 | አ02 | አ03 | አ04 | አ05 | አ06 | አ07 | አ08 | አ09 | አ10 | አ11 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| AMA001 | 3 | 2 | 1 | 3 | 1 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| AMA002 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 |
| AMA003 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 |
| AMA004 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 1 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 |
| AMA005 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 1 | 4 | 3 | 2 | 2 |
| AMA006 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| AMA007 | 4 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 |
| AMA008 | 4 | 1 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 |
| AMA009 | 2 | 4 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| AMA010 | 3 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 |
| AMA011 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 |
| AMA012 | 4 | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| AMA013 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 |
| AMA014 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 |
| AMA015 | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 |
| AMA016 | 3 | 1 | 2 | 2 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 |
| AMA017 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 |
| AMA018 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 |
| AMA019 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 |
| AMA020 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 1 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| AMA021 | 4 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 |
| AMA022 | 2 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 |
| AMA023 | 3 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 1 | 2 | 1 | 3 |
| AMA024 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 |
| AMA025 | 3 | 4 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 1 |
| AMA026 | 2 | 1 | 4 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 |
| AMA027 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| AMA028 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 |
| AMA029 | 3 | 1 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 |
| AMA030 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 |
| AMA031 | 3 | 1 | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 |
| AMA032 | 4 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 1 | 4 | 2 | 1 | 2 |
| AMA033 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 |

## አባሪ ሠ፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት

| ኮድ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| AMA006 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 |
| AMA008 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| AMA009 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 |
| AMA012 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| AMA013 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| AMA014 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 |
| AMA015 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 |
| AMA023 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 |
| AMA027 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| AMA032 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 |